# በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የአስተዳደር ዘርፍ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ግምገማዊ ጥናት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሚያዚያ 2015

<u>አዲስ አበባ</u>

## ማውጫ



| | | ገፅ |
|---|---|---|
| ክፍል አንድ | መግቢያ | |
| 1.1. | የጥናቱ ዳራ | |
| 1.2. | የዘርፉ ተቋማት ሥልጣንና ተግባራት | |
| 1.3. | የጥናቱ ዓላማ | |
| ክፍል ሁለት | በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የአስተዳደር ዘርፍ የሙስና ስጋት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ | |
| ክፍል ሶስት | የጥናቱ ስነ-ዘዴ | |
| 3.1. | የጥናቱ ወሰን | |
| 3.2. | የዝግጅት ምዕራፍ | |
| 3.3. | የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች | |
| 3.4. | የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ | |
| 3.5. | የጥናቱ ተግዳሮቶች | |
| 3.6. | የጥናቱ ውስንነቶች | |
| ክፍል አራት | ዘርፍ-ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና | |
| 4.1. | የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት | |
| 4.2. | ተጠያቂነትን ማስፈን | |
| 4.3. | የተቋማት ግልጽነት | |
| 4.4. | አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ | |
| 4.5. | የንብረት አስተዳደር | |
| 4.6. | የግዥ አስተዳደር | |
| 4.7. | የሰው ሃብት አስተዳደር | |
| 4.8. | የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ | |
| 4.9. | የፕሮጀክቶች አስተዳደር | |
| 4.10. | ኦዲትና ቁጥጥር | |
| 4.11. | የተቋማት የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና | |
| ክፍል አምስት | ምክረ-ሀሳቦች | |
| | ማጣቀሻ ፅሁፎች | |

## ክፍል አንድ፦ መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study)

ሙስና ተለዋዋጭ ባህሪ ያለው ወንጀል ሲሆን፤ በሃገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያስከትል ችግር ነው፡፡ ሌላው ሙስና በአደራ የተሠጠን ኃላፊነት ለግል ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ማስገኛ መሣሪያ አድርጎ መጠቀም ነው፡፡ የሙስና መንሠራፋት የህግ የበላይነትን ያጣምማል፣ የኢኮኖሚ እድገትን ያቀጭጫል፣ የማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነትን ያዳክማል፣ የኢንቨስትመንት ፍሰት ይገታል እንዲሁም ሥርዓት አልበኝነት እንዲንሰራፋ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ሙስናን በብቃት እና በተፈለገው ሁኔታ ለመከላከል፤ አገሮች፣ ዘርፎች ወይም ተቋማት ለሙስና የተጋለጡበትን ስጋቶች መረዳትን ይጠይቃል፡፡ ውጤታማ የሙስና መከላከያ ዘዴዎችን ለመንደፍ እና ለመተግበር መሰረቱ የሙስና ስጋቶችን መገምገም ሲሆን ይህም ተገቢውን የአደጋ መከላከያ እርምጃዎችን ለመለየት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመምረጥ ያስችላል፡፡ እንደዚህ አይነት እርምጃዎች የመንግስት እና/ወይም የግሉ ሴክተር ድርጅቶች ጥረታቸውን እና ሀብታቸውን በጣም አንገብጋቢ እና ተፅእኖ በሚፈጥሩ የትኩረት ቦታዎች ላይ እንዲያውሉ ያስችላቸዋል፡፡

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለበርካታ ዓመታት አስፈላጊ ህጎች እንዲወጡ በማድረግ እና በመተግበር ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ተግባራት ውስጥም ጥናትና ምርምር በማድረግ ሙስናን መከላከል አንዱ ነው፡፡ በኮሚሽኑ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ አደረጃጀቶችና አሰራሮች በዘርፍ ደረጃ ሲተገበሩ የሙስና ሥጋት ተጋላጭነታቸውን በየወቅቱ በመለየት ወቅታዊ መፍትሔ የመስጠት ሥራ በቂ ትኩረት ተሰጥቶታል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ሙስና በየጊዜው እየተከሰተ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር እየሆነ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ኮሚሽኑ ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ሥራን በተቋም ደረጃ የሚከታተሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች እንዲደራጁ በማድረግ ወደ ተግባር ቢገባም፣ እስካሁን በተቋማቱ ውስጥ የሙስና መከላከል ተግባራት የተገኘዉ ዉጤት በሚጠበቀው ደረጃ ላይ ደርሶ አልተገኘም፡፡

በዘርፉ ስር ሊከሰቱ የሚችሉ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአሰራር ስርዓት፣ የግለሰቦች የሥነምግባር ጉድለት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራርብ፤ አያያዝ እና አፈታት ግልፅነት አለመኖር እና የመረጃ አያያዝ ጥራት ችግር ለሙስና የሚያጋልጡ ብልሹ አሠራሮች እንደሆኑ

ይጠቀሳል፡፡ እነዚህና የመሳሰሉት ክስተቶች በተለያዩ ዘርፎች ስር ባሉ ተቋማት ላይ የሚያስከትሉትን የሙስና ተጋላጭነት አደጋ በሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት መመርመር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡

በመሆኑም ይህን የሙስና ሥጋት ችግር በዘላቂነት ለመቀነስ ሲባል በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የአስተዳደር ዘርፍ ስር ከሆኑ 18 ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሆኑ ጉዳዮችን ሙያዊና ስልታዊ የሆነ የተቋማት የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ የሙስና መከላከያ ምክረ-ሀሳቦችን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

## 1.2. የዘርፉ ተቋማት ሥልጣንና ተግባራት

በዘርፉ ስር የተለያዩ በኮሚሽን፣ በባለስልጣን፣ በአስተዳደር፣ በአገልግሎት እና በኢንስቲትዩት ደረጃ የተደራጁ ተቋማት ይገኛሉ፡፡ የተቋማቱ ጥቅል ሥልጣንና ተግባራት እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡

### 1. የፌደራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

- ሀገራዊ የፀረ ሙስና ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ያስፀድቃል፣ አፈፃጸሙን ይከታተላል፣
- የስነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ተግባራትን ለመፈጸም የሚያስችሉ አደረጃጀቶችን በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች እና በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ያደራጃል፣
- የፀረ ሙስና ህጎች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ስለአፈፃጸማቸው የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣
- የክልል የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖችን ያተባብራል፣ አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ያድረጋል፣
- በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የተጋለጡ እና ሊጋለጡ የሚችሉ የአሰራር ስርዓቶችን በማጥናት ወይም እንዲጠኑ በማድረግ የተሰጡ የመፍትሄ /የማሻሻያ/ ሃሳቦችን ያቀርባል፣ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ በማይፈፅሙት ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ ይወስዳል፣
- ኮሚሽኑ ሙስና ለመፈፀም የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ሲጠረጠር ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት ሂደቱ እንዲቋረጥ ወይም አስፈላጊውን ማስተካከያ የማድረግ ስልጣን አለው፡፡ ሆኖም ግን በተደረገው ክትትል ሙስና ስለመፈፀሙ ጥርጣሬ ሲኖረው አግባብነት ላለው ምርመራ አካል ያቀርባል፣
- የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግስት ተሿሚዎች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና የህዝባዊ ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ከተሰጣቸው ኃላፊነት፣ ከመቆጣጠር እና ከመወሰን ስልጣን ጋር በተያያዘ የሚፈጠር የጥቅም ግጭትን ይከላከላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

- የህዝብ ተመራጮችን፣ የመንግስት ተሿሚዎችን እና የመንግስት ሰራተኞችን፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና የህዝባዊ ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁ፣ እንዲያስመዘግቡ፣ ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ፣ መረጃው በአግባቡ ተደራጅቶ እንዲያዝና ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፣
- ለህዝብ ተመራጮች፣ ለመንግስት ተሿሚዎች፣ ለመንግስት ሰራተኞች፣ ለመንግስትና ለህዝባዊ ድርጅት የሥራ ኃፊዎች እና ሰራተኞች የሚያገለግል የስነምግባር ደንብ ያዘጋጃል፣ ያስፀድቃል፣ አፈፃጸሙን ይከታተላል፣
- ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ አካላት ጋር ሀገሪቱን በመወከል ግንኙነት እና ትብብር ያደርጋል፣ በሀገሪቱ ህግ እና ፖሊሲ መሰረት አለም አቀፍ እና አህጉራዊ የፀረ ሙስና ኮንቬንሽኖችን እና ትብብሮች ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ አለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ የፀረ ሙስና ኮንቬንሽኖችን አፋፃፀም በተመለከተ ሀገሪቱን ይወክላል፣
- በስነምግባር ግንባታ እንዲሁም በሙስና ወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ስልጣን የተሰጣቸውን መስሪያ ቤቶች የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ይቀበላል፣

## 2. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

ኮሚሽኑ የሚከተሉትሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፥- የሀገሪቱን የኢንቨስትመንት እድሎች እና ሁኔታዎች ለውጭ እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ማስተዋወቅ፣ ለባለሀብቶች ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታ ለመፍጠር በሚያስፈልጉ የፖሊሲ እርምጃዎች ላይ መንግስትን ማማከር፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እና የሀገር ውስጥ የንግድ ኢንዱስትሪ ትስስርን ማመቻቸት፣ የኢንቨስትመንት፣ የንግድ እና የግንባታ ፈቃዶችን መስጠት፣ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ እና ጥበቃ ስምምነቶችን ከሌሎች ሀገራት ጋር መደራደርና በመንግስት ሲፀድቅ መፈራረም፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነቶችን እና ኤክስፖርትን ያማከለ በፍትሃዊነት ላይ የተመሰረተ የውጭ ኢንተርፕራይዝ ትብብርን ከአገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር መመዝገብ፣ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት እንዲሁም እድሳት፣ ማሻሻያ፣ ምትክ ወይም ስረዛ መስጠት፣ እድሳትን፣ መተካትን፣ እገዳዎችን ወይም ስረዛዎችን ጨምሮ የስራ ፈቃዶችን መስጠት፣ የንግድ ወይም የድርጅት ስም ምዝገባን እንዲሁም መተኪያዎችን ወይም ስረዛዎችን መፈፀም፣ የአንደኛ ደረጃ የግንባታ ተቋራጮችን ደረጃ መስጠት

## 3. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

ከኮሚሽኑ ሀላፊነቶች መካከል በመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ረዳት ክፍሎች ውስጥ ያለውን ድርጅታዊ መዋቅር ማጽደቅ፣ በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ የስራ መደቦችን መመደብ እና ማጽደቅ እና ለሲቪል ሰርቪስ የስራ መደቦች የዕድገት መሰላሎችን መወሰን/ማዘጋጀት ይገኙበታል። በተጨማሪም ኮሚሽኑ ለሚከተሉት መስኮች ሀላፊነት አለበት፥- የሰራተኞች ቅጥር እና አዳዲስ ሰራተኞችን ከድርጅት ስራ ጋር ማቀናጀት፣ ሙያዊ ብቃት እና እውቀትን ለማሳደግ የመንግስት ሰራተኛ ስልጠና፣ የሰራተኞች ደህንነት፣ የዲሲፕሊን እርምጃዎች፣ በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ ጥራትን እና ልህቀትን ማሳደግ፣ የሴቶችን መብት ማሳደግ፣ የላቀ የሥራ ሁኔታን መፍጠር እና ቅሬታዎችን መፍታት፣ መብት ላላቸው ቡድኖች እኩል እድሎችን መስጠት፣ የሰራተኛ የጡረታ መብት፣

## 4. የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን

ኮሚሽኑ የሚከተሉትሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

- ከክልል የፖሊስ ኮሚሽኖች ጋር በመተባበር ስለወንጀል መከላከልና ምርመራ ሀገር አቀፍ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና አንድ ወጥ የሆኑ የአሠራር ደረጃዎችን ያዘጋጃል፤ በመንግሥት ሲጸድቁም ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
- በሕገ-መንግሥቱና በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ፣ በመንግሥትና በሀገር ፀጥታ እና በሰብዓዊ መብት ላይ የሚፈፀሙ ማናቸውም ዓይነት የወንጀል ስጋቶችና ድርጊቶችን ይከላከላል፣ ይመረምራል፤
- የወንጀል ምርመራን በተመለከተ ከፍትህ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በጋራ ይሠራል፤ በፍርድ ቤቶች የሚሰጡትን ትእዛዞችና ውሳኔዎች ይፈፅማል፤
- በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልል ስር የሚወድቁ ወንጀሎችን ይከላከላል፣ ይመረምራል፤
- በፖሊስ ምልመላና ቅጥር፣ በትምህርትና ሥልጠና፣ በማዕረግ አሰጣጥ፣ በደንብ ልብስ አለባበስ፣ በትጥቅና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ሀገር አቀፍ ደረጃዎችን ያወጣል፤
- የሀገሪቱን ጥቅሞች በሚነኩ ጉዳዮች ላይ በውጪ ሀገር የሚፈፀሙ ማናቸውንም ወንጀሎች ከየሀገራቱ ጋር በሚደረግ የጋራ ስምምነት መሠረት ይመረምራል፤ ፖሊስ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አግባብ ካላቸው የውጭ ሀገር መንግስታት ፖሊስ ተቋማትና መንግሥታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ይመሠርታል፤
- የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ ሲከሰትና አስቸኳይ ሁኔታ ሲፈጠር ሠላምና ፀጥታን በማስፈን የተጎዱ ሰዎችን ለመርዳት ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፤

## 5. የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

- በአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነድ ላይ መሪ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ተብለው የተሰየሙ የፌደራል መንግሥት የአስፈፃሚ አካላት በዕቅዳቸው ውስጥ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ማካተታቸውን ያረጋግጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
- በአገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ የአደጋ ሥጋት ስራ አመራር ፖሊሲ እና ስትራቴጂ የትግበራ ዕቅዶችን አሰባስቦ ያደራጃል፤ አፈፃፀሙን በየጊዜው ይከታተላል፣ ይገመግማል፣
- የአደጋ ሥጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ምላሽ እና የአደጋ ተጎጂዎችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ይገመግማል፤

- ለአደጋ ምላሽ ሥራ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ለዕለት ድጋፍ የሚውል ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ ክምችት ይይዛል፣ ያስተዳድራል፤
- ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በሀገር አቀፍ ደረጃ የአደጋ ሥጋት ፕሮፋይል ዝግጅትና ክለሳ ሥራን ይመራል፣ ያስተባብራል፤ የአደጋ ሥጋት ፕሮፋይሉን መሠረት በማድረግ የተሟላ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት በየደረጃው ይዘረጋል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ የተዘረጋው ሥርዓት ተደራሽ፣ ለአደጋ ምላሽ ሰጪና ዝግጁ እንዲሁም ለድንገተኛ ደራሽ አደጋዎች የታቀዱ ዕቅዶች ተግባራዊ መሆን መቻላቸውን ለማረጋገጥ በየደረጃው በተከታታይ ወይም በዕቅድ ላይ ተመስርቶ የናሙና ልምምዶች እንዲከናወኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ የማስተካከያ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤
- የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር በመንግስት የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራተጂዎች፣ የልማት ዕቅዶችና ፕሮግራሞች፣ በግል መሥሪያ ቤቶች ዕቅዶች እንዲሁም በሥርዓተ ትምህርት መካተቱን ያረጋግጣል፣ ከዚህ ጋር በተያያዘም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ያደርጋል፤
- የመረጃና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ሥራ በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤ በብሔራዊ ደረጃ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣ እንዳስፈላጊነቱ የክልል መስተዳድሮች ተመሳሳይ የመረጃ ማዕክል እንዲያቋቁሙ ድጋፍ ያደርጋል፤
- አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱ ሕጎች መሠረት ለብሔራዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ትግበራ አመች ሁኔታን ለመፍጠር አግባብነት ካላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና የመንግስትና የግል መሥሪያ ቤቶች ጋር የሥራ ግንኙነት ይፈጥራል፣ ይተባበራል፤

## 6. የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር

የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

- የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ እቅድን ለማስፈጸም ቀልጣፋና ብቃት ያለው አሠራር ይዘረጋል ይተገብራል፤
- የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ መዋጮ አሰባሰብ ሥርዓት ያዘረጋል፣ መዋጮ ይሰበስባል፣ በሚመለከተው የመንግሥት አካል በሙሉ በተገቢው ጊዜና መጠን መሰብሰቡን ያረጋግጣል፣ አሠሪ መሥሪያ ቤቶች ሥርዓቱን ተግባራዊ ማድረጋቸውን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሲሆን ሰነዶችንና መዛግብትን አስቀርቦ ወይም በአሠሪ መሥሪያ ቤቶች ተገኝቶ ይመረምራል፤
- የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንዶችንና ከፈንዶቹ ጋር የተያያዙ ሀብቶችን ያስተዳድራል፤
- የመንግሥት ሠራተኞችን ለጡረታ መብት ብቁ የሚያደርጉ ማስረጃዎችን በቅድሚያ አሰባስቦ ይይዛል፤
- የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የጡረታ መዋጮ ሂሣብ መዝገብ በማይዙ፣ ማስረጃ በማይልኩ እና መረጃ በማይሰጡ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ግለሰቦች ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

- የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ መብት ለማስከበር የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ብቃት እና ተቀባይነት፣ የጥቅም ዓይነት እና መጠኑን ይወሰናል፣ ክፍያ ይፈጽማል፤
- የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ መብትና ጥቅም ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤
- የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንዶችን በትሬዠሪ ቦንዶችና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰኑ ትርፋማና አስተማማኝ በሆኑ ሌሎች ኢንቨስትመንቶች ላይ ያውላል፤

## 7. የግል ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር

የግል ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

- የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ዕቅድን ለማስፈጸም ቀልጣፋና ብቃት ያለው አሠራር ይዘረጋል፣ ይተገብራል፤
- የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ መዋጮ አሰባሰብ ሥርዓት ይዘረጋል፣ መዋጮ ይሰበስባል፣ በሚመለከተው የመንግሥት አካል በኩል በተገቢው ጊዜና መጠን መሰብሰቡን ያረጋግጣል፣ የግል ድርጅቶች ሥርዓቱን ተግባራዊ ማድረጋቸውን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሲሆን ሰነዶችንና መዛግብትን አስቀርቦ ወይም በግል ድርጅቶች ተገኝቶ ይመረምራል፤
- የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ፈንዶችንና ከፈንዶቹ ጋር የተያያዙ ሀብቶችን ያስተዳድራል፤
- የግል ድርጅት ሠራተኞችን ለጡረታ መብት ብቁ የሚያደርጉ ማስረጃዎችን በቅድሚያ አሰባስቦ ይይዛል፤
- የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የጡረታ መዋጮ ሂሣብ መዝገብ በማይዙ፣ ማስረጃ በማይልኩ እና መረጃ በማይሰጡ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤
- የግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ መብትን ለማስከበር የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ብቃትና ተቀባይነት፣ የጥቅም ዓይነት እና መጠኑን ይወስናል፣ ክፍያ ይፈጽማል፤
- የግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ መብትና ጥቅም ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤
- የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድን በትሬዠሪ ቦንዶችና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰኑ ትርፋማና አስተማማኝ በሆኑ ሌሎች ኢቨስትመንቶች ላይ ያውላል፤
- የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ በየተወሰነ ጊዜ በሂሣብ ስሌት አዋቂዎች እንዲጠና ያደርጋል፤
- የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፕሮግራሞች ስለሚጠናከሩበት ሁኔታ ጥናት እያካሄደ ለመንግሥት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

## 8. የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር

**አስተዳደሩ** የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

- የኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ብሔራዊ የፖሊሲ፣ የህግ፣ የስታንዳርድ እና ስትራቴጂ ረቂቆችን የማዘጋጀትና ሲጸድቁም ተፈጻሚነታቸውን የመከታተል፣
- በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረቱ የኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ደህንነት ምርቶችን እና አገልግሎቶችን የማበልጸግና ስራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ፣
- መንግስታዊ እና የግል ተቋማት አገራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ፖሊሲ እና ስታንዳርድ ማዕቀፎችን ተከትለው የየራሳቸው ፖሊሲና ስታንዳርድ ቀርጸው ስራ ላይ እንዲያውሉ ድጋፍ የመስጠትና አፈጸጸማቸውን የመቆጣጠር፣
- ኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ባደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ወይም ስርዓቶች ላይ ወይም በዜጎች ስነልቦና ላይ የሚሰነዘሩትን የሳይበር እና ኤሌክትሮማግኔቲክ ጥቃቶችን ለመከላከል አስፈላጊ አጸፋዊ እርምጃ የመውሰድ፣
- በማንኛውም ወቅት የኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ደህንነት ኦዲት የማድረግ፣ መመዘኛውን አሟልተው ለተገኙ ተቋማትም የደህንነት ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የመስጠት ወይም እነዚህን ተግባራትእንዲያከናውኑ ለሌሎች ተቋማት ውክልና የመስጠት፣
- ወደ አገር የሚገቡና ከአገር የሚወጡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎች፣ የመረጃ አነፍናፊዎች እና የጥቃት ቴክኖሎጂዎች በአገር ደህንነት ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን አደጋ ከመከላከል አንጻር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የመቆጣጠር፣
- በተመረጡ ድንበር ዘለል የብሔራዊ ደህንነት ስጋት እንቅስቃሴዎች ዙሪያ መረጃ የመሰብሰብ፣ የመተንተን፣ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ እንዲሁም ለፀጥታ ሃይሎች ድጋፍ የመስጠት፣
- አገራዊ አቅም ባልተፈጠረባቸው ክፍተቶች ደህንነታቸው የተጠበቁ የኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት መሰረተልማቶችን እና ስርዓቶችን የማበልጸግና የመዘርጋት፤ እንዲሁም ለሚያቀርበው ምርትና ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ ክፍያ የማስከፈል፣

## 9. የቤተ-መንግስት አስተዳደር

የቤተ-መንግስት አስተዳደር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦ ብሔራዊ ቤተመንግሥትንና ይህ አዋጅ እስከፀናበት ድረስ በሥሩ የቆዩትን ቤተመንግሥቶችና ሌሎች በፌደራል መንግሥት የሚቋቋሙ ቤተመንግሥቶችን ያስተዳድራል፣ የቤተመንግሥት ቅርሶችን ይንከባከባል፣ እንዳስፈላጊነቱ እንዲጠገኑ ያደርጋል፣ የቤተመንግሥት ተቋሞችና ቅርሶች ደህንነታቸው በማይጎዳ ሁኔታ የቱሪስት መስህብ ሆነው እንዲያገለግሉ ያደርጋል፣ በቤተመንግሥት የሚደረጉ የመንግሥት መስተንግዶዎችን ያስተባብራል፣ ያስፈጽማል፤

## 10.የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት

የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ከተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነቶች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፦ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት የሚመለከታቸውን ተቋማት የማስተባበር፣ የሚደርሱትን መረጃዎች የማደራጀት እና የመተንተን ስራ ይሰራል፣ በወንጀል

ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በሚመለከቱ የሕግ፣ የቁጥጥርና የፖሊሲ ማሻሻያዎች ላይ መንግሥትን ያማክራል፣ በሚስጥር የሚጠበቁትን ሳይጨምር በተቋቋመበት አዋጅ መሠረት የተቀበላቸውን ሪፖርቶች፣ ለሕግ አስፈጻሚ አካላት የተመሩ ጉዳዮች፣ ከተመሩት ውስጥ ክስ የተመሠረተባቸው የወንጀል ጉዳዮች፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የቀረቡ የእርዳታ ጥያቄዎችና የመሳሰሉ ስታትስቲክሳዊ የቁጥር መረጃዎች ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፣ ማዕከሉ በሚስጥር የሚጠበቁትን ሳይጨምር ወቅታዊ የሆኑ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በተመለከተ የተከሰቱ የመፈጸሚያ ዘዴዎችንና ሌሎች ጥርጣሬ የሚፈጥሩ ግብይቶችን ለማወቅ የሚረዱ መረጃዎች ኃላፊነት ላለባቸው ሰዎች እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው ያሰራጫል፣

## 11.የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት

የየስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ቁልፍ ተልዕኮ የስደተኞችን አካላዊ ደህንነት መደገፍ እና መጠበቅ እንዲሁም ስደተኞች ለችግር ዘላቂ መፍትሄ እስኪያገኙ ድረስ በክብር እንዲኖሩ ማድረግ ነው:: በተጨማሪም የሚከናወኑ የስደተኞች ፕሮግራሞችን በመሪነት ደረጃ ማስተባበር እና ማስተዳደር ነው:: የሚከተሉት ግዴታዎች ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራትን ያጠቃልላል፡- በሁሉም የስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ጉዳዮች ላይ እንደ ቁልፍ የመንግስት ኤጀንሲ እና ተወካይ ሆኖ ማገልገል፣ የስደተኝነት መስፈርቶችን ማውጣት እና መወሰን፣ የስደተኛ ካምፖችን ማቋቋም እና አጠቃላይ የካምፕ ተግባራትን ማስተዳደር፣ አካላዊ ጥበቃን መስጠት እና የሁሉንም አሳሳቢ ሰዎች ደህንነት መጠበቅ፣ ለስደተኞች መሰረታዊ እና ማህበራዊ አገልግሎት መስጠትና ማስተባበር፣ በሀገር ደረጃ የስደተኞች ድጋፍ ፕሮግራሞችን ማስተባበር፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አጋሮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተግባራቶቻቸውን እንዲፈጽሙ መርዳት እና ማመቻቸት፣ የስደተኞች መፈናቀል መንስኤዎች ሲቀረፉ ወደ አገራቸው የመመለስ እንቅስቃሴዎችን ማመቻቸት እና ማካሄድ፣

## 12.የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት

ከአገልግሎቱ ሥልጣንና ተግባራት የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- ከህዝብ ሰላምና ደህንነት፣ ከታላላቅ ሀገራዊ ክንዉኖች፣ ከተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ አደጋዎች፣ ከዘመቻ ስራዎች፣ ወዘተ ጋር በተያያዘ በየደረጃዉ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረቱ አጀንዳዎችን መቅረጽ፣ ማሰራጨትና በመሰረታዊ ጉዳዮች ዙሪያ መግባባትን መፍጠር፣
- የመንግሥት አጀንዳና አፈፃፀሞችን ተደራሽ የሚያደርጉ በጠንካራ አደረጃጀትና ኔትዎርኪንግ የተደገፈ የዲጂታል ሚዲያ አሰራር መዘርጋት፣

- የመንግሥትን ፖሊሲ፣ መርህ እና ዕቅድ መሠረት በማድረግ ማኅበረሰብን ተደራሽ የሚያደርጉ አጀንዳዎችን ማዘጋጀት፣ እንዲሁም የማኅበረሰብን ሁለንተናዊ ተሳትፎ የሚያሳድጉ ንቅናቄዎችን መፍጠር፣
- የመንግሥትን ፖሊሲ፣ መርሕና ዕቅድ መሠረት በማድረግ፤ እንዲሁም ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን፣ ሀገራዊ ተግባቦትን፣ የዲሞክራሲ ባህል መጎልበትን፣ ሁለንተናዊ ብልጽግና መፍጠርንና የመሳሰሉትን መሠረት በሚያደርግ ማዕቀፍ ሚዲያዎችን መምራት፣
- ከሕዝብ ሰላምና ደኅንነት፣ ከታላላቅ ሀገራዊ ክንውኖች፣ ከተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ፣ ከዘመቻ ሥራዎች፣ ከግጭቶች እና ከመሳሰሉት ጋር በተያያዘ በሚዲያ አዝማሚያዎች ዳሰሳና በህዝብ አስተያየት ጥናቶች መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን፣ ድምዳሜዎችን ለባለድርሻ አካላት ማሳወቅና አገልግሎት ላይ እንዲዉል ማድረግ፣
- በተተነተኑ፣ በተደራጁና ይዘታቸዉ በታወቀ መረጃዎች ላይ በመመሥረት ጋዜጣዊ መግለጫዎችን፣ ጋዜጣዊ ጉባዔዎችንና ምላሾችን እንደ አስፈላጊነቱ ማዘጋጀት፣
- የቅድመ ቀዉስ ትንተና በመስራት፣ እንዲሁም ድንገት በሚፈጠሩ አደጋዎችና ግጭቶች ዙሪያ መረጃዎችን በፍጥነት በማሰባሰብና በማደራጀት ትክክለኛውን መረጃ በፈጣን መንገድ ለባለድርሻ አካላትና ለዜጎች ማቅረብ፣
- በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ኢትዮጵያን በሚመለከት የሚወጡ የሚዲያ መረጃዎችን ዳሰሳ በመሥራት ለጠቅላይ ሚኒስትር ማቅረብ፣ ከዳሰሳው መረጃዎች ላይ በመነሣትም አስፈላጊውን የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ መቅረፅ፣

## 13.የኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ባለስልጣን

የኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ባለስልጣን ተልዕኮ፥ በኢትዮጵያ ያለውን የኮሙዩኒኬሽን ዘርፍ በግልፅና በብቃት ለመቆጣጠር እና ተደራሽነትን ለማሳደግ እንዲሁም የተጠቃሚዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ በሁሉም የኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች ፍትሃዊ ተወዳዳሪ አሰራርን በማረጋገጥ ጥራት ያለው የኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ መስጠት ነው:: ከባለስልጣኑ ስልጣኖች እና ተግባራት የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፥- የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የፖስታ እና የጥቅል አገልግሎቶችን ጨምሮ በኮሚዩኒኬሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ፈቃድ መስጠት እና የኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት ኦፕሬተሮችን መቆጣጠር፣ የኮሙዩኒኬሽን አገልግሎቶች አቅርቦት የቴክኒክ ደረጃዎችን መወሰን፣ ከአገልግሎቶች ጋር የተያያዙ ታሪፎችን መቆጣጠር እንዲሁም የአገልግሎቶች ተጠቃሚዎችን ጥቅም ማስጠበቅ፣ ከቴሌኮሙኒኬሽን አውታረመረብ ጋር ሊገናኙ የሚችሉ የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎችን መቆጣጠር፣ በኢትዮጵያ የራዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀምን መቆጣጠር፣ የመረጃ ደህንነትን፣ የውሂብ ግላዊነትን (data privacy) እና ጥበቃን ማሳደግ፣ የኮሙዩኒኬሽን አገልግሎቶች ከተቀመጡት የጥራት ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የፈቃድ ወሳጆችን እንቅስቃሴ መከታተል፣በስራ ላይ የዋሉ የቁጥጥር ህጎችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ጨምሮ የፍቃድ ውሎች እና ሁኔታዎች (license terms and conditions) ማክበራቸውን መቆጣጠር፣

## 14.አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ተልዕኮ ሰላምና ብልጽግና የሰፈነባት ሀገር ለማብቃት እና ለማነቃቃት በሀገር አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለው የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ስነ-ምህዳር እድገትን ማምጣት ነው፡፡ ከተሰጡት ኃላፊነቶች የሚከተሉት ይገኙበታል፦ በጥናት ላይ የተመሰረቱ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ አገልግሎቶችን እና ምርቶችን ማቅረብ፣ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ምርምር እና ልማት ፕሮግራሞችን የሚያግዙ ሀገራዊ መሠረተ ልማቶችን ማደራጀት፣ ከብሄራዊ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ጋር ተዛማጅ ፖሊሲዎችን፣ ህግ እና የቁጥጥር ማዕቀፎችን ማዘጋጀት፣ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ምርምር፣ ልማት እና ስምሪት ላይ የግል ተነሳሽነቶችን መደገፍ፣ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራሞችን የሚደግፍ እንዲሁም ከመከላከያ እና ከሀገር ደህንነት ጋር ለተያያዘ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚያገለግል መሆኑን ማረጋገጥ፣ የብሔራዊ ዳታቤዝ ልማት እና አጠቃቀምን ማመቻቸት፣ ከከፍተኛ ተቋማት ጋር በትብብር በመስኩ የሰው ኃይል ልማትን ማገዝ፣

## 15. የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

ለህዳሴው ጉዞ በንድፈ ሃሳብ ዕውቀት የዳበረ፣ በአመለካከትና ክህሎት የጎለበተ፣ የሥራ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ያለው አመራር ማዘጋጀት፣ ለአካዳሚው ዓላማ መሳካት በአገራዊ፣ በአካባቢያዊ፣ በአህጉራዊ እና በዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ላይ በቂ ዕውቀት ያላቸው፣ በሥነምግባር የታነጹ፣ የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ያላቸው ብቁ መምህራን መልምሎ ማዘጋጀት፣ በልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ፍልስፍና ዙሪያ ለአገር ውስጥና ለውጭ ለተለያዩ የአመራር አካላትና ባለሙያዎች ሥልጠና መስጠት፤ የሠልጣኙን ግንዛቤ፣ ዕውቀትና ክህሎት የሚያሳድጉና ለችግሮች አፈታት የሚረዱ የተመረጡ ልምዶችን በመቀመር ሥልጠና መስጠት፣ የመንግሥት ፖሊሲዎችን አተገባበርና ውጤታማነት ማጥናት፣ በቅድመ ሥልጠና፣ በሥልጠና ላይና ከሥልጠና በኋላ ክትትል ማድረግ፣ የብቃትና ጥራት ደረጃን መለካት፤ ያጋጠሙ ችግሮችን በጥናትና ምርምር በማስደገፍ ግኝቶቹን ለሥልጠና በሚመጥን መልኩ በግብዓትነት ማቅረብ፣ ተመጋጋቢነትና ቀጣይነት ያለው የአመራር ግንባታ ሥርዓት በመዘርጋት በየደረጃው ያለውን አመራር አገራዊ፣ አካባቢያዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ አውድ ላይ አቅማቸውን መገንባት፣

## 16.የኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት

የኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት ተልዕኮ የመንግስት፣ የግል እና ሌሎች ድርጅቶች ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ዘመናዊ ብቃትን መሰረት ያደረገ የስልጠና፣ የማማከር፣ የምርምር እና የብቃት ምዘና አገልግሎት መስጠት ነው፡፡ ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል፦ ፍላጎትን እና ዘመናዊ ብቃትን መሰረት ያደረጉ የአስተዳደር ልማት ስልጠናዎች፣የማማከር እና የደንበኛ ድርጅቶችን ችግር መፍታት የሚችሉ የምርምር አገልግሎቶችን መስጠት፣ በሀገሪቱ ውስጥ ከሚሰሩ ተመሳሳይ የሀገር ውስጥ እና አለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ልዩ የስልጠና ፕሮግራሞችን ቀርጾ መስጠት፣ ችግር ፈቺ (ተግባራዊ) ጥናቶችን፣ የተግባር ተኮር ጥናቶችን እና የምርመራ ምዘናዎችን (diagnostic assessments) ማካሄድ እና ተገቢውን ቀጣይ እርምጃ መምከር፣ ብቁ የሆኑ አዳዲስ ስራተኞችን

ለመቅጠር ለሚፈልጉ ድርጅቶች ብቃትን መሰረት ያደረገ የምዘና አገልግሎት መስጠት፣ የራሳቸውን አሰልጣኞች በመጠቀም ስልጠናዎችን ለመስጠት ወይም አውደ ጥናቶችን እና ሌሎች ውይይቶችን ለማካሄድ ለሚፈልጉ ደንበኞች የፋሲሊቲ አገልግሎት መስጠት፣

**17. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዓላማዎቹን ለማሳካት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

- ሕጋዊ ገንዘብን የመቅረጽ፣ የማተም ወይም የማስቀረጽ፣ የማሳተምና የማሠራጨት፣
- በሕጋዊ መንገድ የወጡትን ሣንቲሞችና የገንዘብ ኖቶችን ማስወገድ ወይም እንዲወገዱ የማድረግ፣
- የገንዘብና ብድር አቅርቦት በተፈለገው መጠን መገኘትን፣ እንዲሁም የወለድ ተመንና ሌሎች ክፍያዎችን የመወሰንና የመቆጣጠር፣
- የውጭ ምንዛሪ ተመን ፖሊሲ የመቅረጽና ተግባራዊ የማድረግ፣
- የኢትዮጵያን የዓለም አቀፍ መጠባበቂያ ሂሣቦች የማስተዳደርና የመምራት፣
- ለባንኮች፣ ለመድን ሰጪዎችና ለሌሎች የገንዘብ ተቋማት ፈቃድ የመስጠትና ሥራቸውን የመቆጣጠር፣
- ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት የአጭርና የረጅም ጊዜ የብድር አገልግሎት እንደ አስፈላጊነቱ እንዲያገኙ የማድረግ፣
- ማናቸውም ዓይነት ተቀማጭ ገንዘብ ከውጭ አገር ምንጮች የመቀበል፣
- ከማንኛውም ሰው መረጃዎችን በመሰብሰብ የክፍያ ሚዛን፣ የገንዘብ አቅርቦትና የዋጋ ትንበያዎችን እንዲሁም ለትንተናና የገንዘብ፣ የቁጠባና የምንዛሪ ፖሊሲዎችን ለመቅረጽና ለመወሰን የሚረዱትን ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ጠቋሚ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የያዘ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ጠቃሚ የሆኑ ጥናቶችን በየጊዜው የማካሄድ፣
- መንግሥትን በባንክ አገልግሎት፣ በገንዘብ ውክልናና በፋይናንስ አማካሪነት የማገልገል፣
- ኢትዮጵያ የተዋዋለቻቸውን ዓለም አቀፍ የገንዘብና የባንክ ስምምነቶች በማክበር የመሥራትና አገሪቱን በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እንዲሁም በሌሎች በማዕከላዊ ባንኮች በተቋቋሙ ዓለምአቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ዘንድ የመወከል፣

18.**የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት**

በአብዛኛው የፕሮቶኮል ስራዎችን የሚሰራ ተቋም ነው::

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

**አጠቃላይ ዓላማ፡-**

በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የአስተዳደር ዘርፍ ተቋማትን የአሰራር ስርዓት ከሙስና ስጋት አንፃር በመገምገም የሙስና ተጋላጭነት ትንተና ማካሄድ ነው::

**ንዑስ አላማዎች፡-**

የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የአስተዳደር ዘርፍ ተቋማትን፡-

- የአሠራር ስርዓቶች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣
- የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማስቀመጥ፣

## ክፍል ሁለት፦ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የአስተዳደር ዘርፍ የሙስና ስጋት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ

በኮሚሽን ደረጃ የተደራጁ ተቋማት የተለያዩ መስሪያ ቤቶችን ሥራ የማቀናጀት፣ ፖሊሲን እና ስትራቴጂን የመቅረፅና አፈጻጸሙን በበላይነት የማስተባበር እንዲሁም መስሪያ ቤቶችን የማስተባበር ጥቅል ሥልጣንና ተግባራት አሏቸው፡፡ ከፖሊሲ ጉዳዮች አንፃር የሚያጋጥሙ ብልሹ አሰራሮች ላይ ያተኮሩ ጥናቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሙስና የህዝብ አለመተማመንን የሚፈጥር እና ዋና ተግባራትን እና ተልዕኮዎችን የመፈጸም ድርጅታዊ አቅምን የሚያዳክም ስጋት ነው፡፡ ሙስና በመንግስት ሴክተር ተግባራት ላይ ጣልቃ በገባ ቁጥር ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ትግበራዎችን እያጣመመ ይሄዳል (Knies et al., 2016)፡፡ በቢዝነስ እና በፖለቲካ መካከል ያለው ለኪራይ ሰብሳቢነት የሚያጋልጥ የተበላሸ መጠላለፍ ላይ ያተኮሩ ፅንሰ-ሀሳቦች፣ ይህ መጠላለፍ ብርቱ (dynamic) ቢዝነሶችን፣ ፉክክርን እና የስራ ፈጠራን እንደሚያደናቅፍ እንዲሁም ደካማ ቁጥጥር እና የዕምነት ማጣት እንደሚያመጣ አስምረውበታል (Folsom, 2003)፡፡

ሌላው ደግሞ የፖሊሲ እገታ (policy capture) ነው፡፡ ይህ ጉዳይ የፖሊሲ ውሳኔዎችን ለሕዝብ ጥቅም ከማዋል ይልቅ ወደ አንድ የተወሰነ ጥቅም ቡድን ወይም ሰው ፍላጎት በቋሚነት እና በተደጋጋሚ የመምራት ሂደት ነው፡፡ ይህም የልዩ ፍላጎት ቡድኖችን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል በተግባር ላይ የማይውሉ (የታገዱ) ማሻሻያዎችን ወይም በበቂ ሁኔታ ያልተተገበሩ ፖሊሲዎችን ሊያስከትል ይችላል፡፡ የሕዝብ ጥቅምን ወደጎን በመተው በመካሄድ ላይ ያሉ ማሻሻያዎችን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ መቀየርም ይችላል (OECD, 2017)፡፡ ይህ የፍላጎት ቡድኖች ድብቅ እና ቀስቃሽ ተጽእኖ ደንቦችን እና እራሱ አስፈጻሚውን 'በማገት' ሴክተሮችን እና አገልግሎቶችን በቁጥጥር ስር ለማዋል ያስችላቸዋል፡፡ ለመንግስት ባለሥልጣናት ጥቅማጥቅሞችን በመስጠት የግል ጥቅሞችን ለማመንጨት ባለመ መልኩ ለተከበቡ ኔትወርኮች ጥቅም የመገዛት ሂደት ወደ ደንቦች፣ አዋጆች እና ሂደቶች ሲደርስ ቁጥጥር እና ስልጣን ለግለሰቦች፣ ቡድኖች ወይም ድርጅቶች የግል ፍላጎቶች ማራመጃ ሆኑ ማለት ነው (Esposito, 2010; Shah, 2007)፡፡

የፖሊሲ አውጪዎችን እና የመንግስት ሰራተኞችን ማበረታቻ (incentives) በማዛባት፣ ሙስና የመንግስት ፖሊሲዎችን ጥራት እና ውጤታማነት ይጎዳል፡፡ እንደ ጥራት ያለው የህዝብ መሠረተ

ልማት እና ትምህርት አቅርቦት ያሉ ዋና ዋና የህዝብ አገልግሎቶች በከፍተኛ ሁኔታ ሊደናቀፉ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ መንግስታት የኢኮኖሚ እድገትን ለማምጣት እና ድህነትን ለመቀነስ በሚያደርጉት ጥረት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አለው (Gupta et al., 2000)፡፡ በተጨማሪም መንግስታት የመበደርም ሆነ የፋይናንስ ስጋቶችን የመቆጣጠር አቅማቸው በሙስና እና በሌሎች ተቋማዊ ድክመቶች ሊዳከም ይችላል፡፡ ሙስና የገቢ ማሰባሰብን በመጉዳት  መንግስታት የዕዳ ግዴታቸውን ለመወጣት የሚያደርጉትን ጥረት የበለጠ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ አንዳንድ ጥናቶች ደካማ ተቋማት እና ደካማ ፖሊሲ ያላቸው አገሮች ብዙ ጊዜ ዕዳቸውን በወቅቱ ለመክፈል እንደሚቸገሩ ያሳያሉ (IMF and World Bank, 2012)፡፡

በባለስልጣን ደረጃ የተደራጁ ተቋማት የሚከተሉት ጥቅል ሥልጣንና ተግባራት አሏቸው፥- የቁጥጥር ደረጃ የማውጣትና በወጣው ደረጃ መሠረት መተግበሩን የማረጋገጥ፣ በዋናነት በተሰጠው የዘርፍ ሥራ ስታንዳርዶችን የማውጣት፤ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ የቁጥጥር ሥራ የማከናወን፣ ወይም በሚመለከተው አካል የወጡ ስታንዳርዶችን የማስፈጸም፣ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲኖሩ ፈቃድ የመስጠት እና የመቆጣጠር ሥራን የማከናወን፡፡ ከፈቃድ እና ደረጃ አሰጣጥ ጋር የተገናኙ የሙስና ክስተቶችን የተመለከቱ ጥናቶች ከታች በጥቂቱ ቀርበዋል፡፡

የስራ ፈቃዶች (permits) እና ላይሰንሶች የንግድ እና የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን የተመለከቱ ደንቦችን ለፈጸሙት ብቻ ለመገደብ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ለምሳሌ የግንባታ ፈቃዶች የሚሰጡት የሕንፃ ግንባታ ዕቅዶች ከሕጎች እና ደንቦች ጋር ሲጣጣሙ ብቻ ነው፡፡ የሚገኘው ከፍተኛ ገቢ አንዳንድ ጊዜ ለባለሥልጣናት ከሚሰጠው ልዩ የመወሰን ስልጣን (discretionary power) ጋር ተዳምሮ የፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ለሙስና የተጋለጠ ነው፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚባለው ጉዳይ ብልሹ ድርጊቶች የሚፈጸሙት ፈቃድ ሲሰጥ ብቻ ሳይሆን ሲተገበር ወይም ሲረጋገጥ ጭምር መሆኑ ነው፡፡

Simon et al. (2017) የሰሩት ጥናት እንደሚያሳየው በህንድ ውስጥ ፈቃዶችን ማግኘት በኩባንያ እና በመንግስት ባለስልጣናት መካከል ጉልህ የሆነ መስተጋብር (interaction) በመኖሩ ምክንያት ለከፍተኛ የሙስና ስጋት የተጋለጠ ነው፡፡ አንድ ኩባንያ ምን ዓይነት ፈቃዶች ማግኘት እንዳለበት ደካማ ዕውቀት፤ ለቢሮክራሲያዊ መሰናክሎች አለመዘጋጀት እና እነሱን ለማሸነፍ የሚወስደው ጊዜ እንዲሁም የተወሰነ ልምድ ያለው ወይም ምንም ልምድ የሌለው ሰው ሂደቱን እንዲቆጣጠር ማድረግ ለስጋቱ መከሰት አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

በጋና ውስጥ ባለው የንግድ ምዝገባ ሥርዓት ውስጥ የታወቀው ትልቁ ፈተና አንድ ሰው ንግድ ለመጀመር የሚያስችለውን ፈቃድ እና የምስክር ወረቀት ለማግኘት ያለው መዘግየት ነው፡፡ አንድ ጥናት እንደሚያሳየው እነዚህ መዘግየቶች በጋና ውስጥ ባለው የንግድ ምዝገባ ሥርዓት ውስጥ ለአስተዳደራዊ ሙስና ዋና መንስኤ ናቸው፡፡ በንግድ የምዝገባ ስርዓት ላይ የሚስተዋሉ መዘግየቶችን ለማስወገድ እንዲሁም ያለውን አስተዳደራዊ ሙስና ለመከላከል እና ለመዋጋት

የአገልግሎት አሰጣጥ ቻርተሮችን እና የአውቶሜሽን አገልግሎቶችን መተግበር እንድሚገባ ምክሮችን ሰጥቷል (CKB Kasser-Tee, 2020)።

አንድ ጥናት እንደሚያሳየው በጆርጂያ ከ2003 በፊት ፓስፖርት ለማግኘት፣ ንብረት ለመመዝገብ፣ ንግድ ለመጀመር ወይም ፈቃድ ለማግኘት ጉቦ ያስፈልግ ነበር። የአስተዳደራዊ ሂደቶች መብዛት የመንግስት ባለስልጣናት ከሚከፈላቸው እጅግ ዝቅተኛ ደመወዝ ጋር ተዳምሮ በሀገሪቱ ለሙስና ትልቅ መነሳሳትን ፈጥሯል። ስለዚህ የአሰራር ሂደቱን ለማፋጠን ወይም መስፈርቶችን ለማለፍ ብዙ ጊዜ ጉቦ ይከፈል ነበር (World Bank, 2012)።

በላትቪያ የተደረገ ጥናት የግንባታ ፈቃድ መቀበልን የሚቆጣጠሩት መደበኛ ደረጃዎች፣ ህጎች እና ደንቦች ግልጽ ያልሆኑ፣ የሚቃረኑ እና አንዳንዴም ለማሟላት የማይቻሉ መሆናቸውን አረጋግጧል። ይህ ሆኖ ሳለ በፈቃጁ እና በግንባታ ፈቃድ ተቀባዩ መካከል ምንም ዓይነት ግጭቶች ወደ ፍርድ ቤት አይወሰዱም። ጥናቱ ለዚህ ግኝት ማብራሪያ ይሰጣል - አለመግባባቶችን ለመፍታት ወይም ለማስወገድ የሚኬድበት መንገድ በኦፊሴላዊ ደንቦች፣ ደረጃዎች እና ህጎች ሳይሆን የተለያዩ ብልሹ አሰራሮችን በመጠቀም ነው (Sedleniekson, 2003)።

የደን ምንጣሮ ፈቃድ (logging permits) ለማግኘት ድርጅቶች ለደን ባለሥልጣኖች ስልታዊ ጉቦ እንደሚከፍሉ ማሌዢያ፣ ላኦስ እና ኢንዶኔዢያን ጨምሮ በመላው እስያ ፓስፊክ ክልል ውስጥ ተዘግቧል። በህገ-ወጥ መንገድ የፈቃድ ግዥ እና ሌሎች ብልሹ ተግባራት ላይ ቅሬታዎች ሲነሱ መንግስታት አንዳንድ ጊዜ ከዜጎቻቸው ይልቅ ለኩባንያዎች በመወገን ውሳኔ ሲሰጡ ይስተዋላል። ከደን ጋር የተገናኘ ፈቃድ የሚሰጥበት አካሄድ ብዙውን ጊዜ የፖለቲካ ልሂቃን ከኩባንያዎች የገንዘብ ጥቅማጥቅሞችን ከሚያገኙበት የጥቅም መደጋገፍ (patronage) ስርዓቶች ጋር የተቆራኘ ነው (Transparency International, 2010) ።

ፈቃዶች ወይም የመጠቀም መብቶች (access rights) በዱር እንስሳት አስተዳደር እና ንግድ ውስጥ ከሚከሰቱ ብልሹ አሰራሮች አንድ አካል ናቸው። በባለስልጣናት እና በፈቃድ ወሳጆች/ ተቀባዮች መካከል በሚደረገው መስተጋብር ምክንያት ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው። ሙስና ዘላቂ ያልሆነ እና ህገወጥ የዱር እንስሳት ንግድን በማምጣት፣ የፖሊሲዎች እና ደንቦች ንድፍ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደር እንዲሁም የህዝብን ሃብት ወደ ግል ኩባንያዎች እና ግለሰቦች ኪስ በማዛወር (ወደ ህዝብ አገልግሎትና ጥበቃ መመለስ የነበረበትን ገቢ በማሳጣት)፣ የዱር እንስሳት ንግድን በተገቢው መንገድ ለመቆጣጠር እየሰሩ ያሉትን መንግስታት፣ አለም አቀፍ አካላት፣ ኩባንያዎች እና የሲቪል ማህበረሰብን ምርጥ ጥረቶችን ይጎዳል (Zain, 2020)።

በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚከሰቱ ሙስና አደጋዎች እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ በሰፊው የሚያመለክተው መንግስታት (አካባቢያዊ፣ ማዘጋጃ ቤት ወይም ሀገር አቀፍ) ለዜጎቻቸው የሚሰጡትን አገልግሎቶች ነው። እንደ ጤና አጠባበቅ፣ ትምህርት፣ ውኃ እና ሳኒቴሽን፣ ቴሌኮሙዩኒኬሽን፣ ፈቃድ እና ሌሎች በመንግስታት ወይም

በግል አካላት (ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የግል ድርጅቶች፣ ወዘተ) አማካኝነት ለዜጎች ጥቅም የሚሰጡ አገልግሎቶች አቅርቦትን ያጠቃልላል።

በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚፈጸሙ አንዳንድ ሙስና ዓይነቶች የሕዝብ አገልግሎት እኩል ተጠቃሚነት ሰብዓዊ መብትን ይገፋሉ፣ እንዲሁም የዜጎችን ተደራሽነት የሚጥሱ መሠረታዊ ኢ-ፍትሃዊነትን ያባብሳሉ። በዚህም በይበልጥ የተገለሉ እና ውክልና የሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ይጎዳሉ (Chêne, 2014)። ከዚህም በላይ የሙስና መንሰራፋት የአገልግሎት አሰጣጡን ሰንሰለት መበላሸት ሊያስከትል ስለሚችል የመንግሥት መዋቅር ዜጎቹን የመጠበቅ ግዴታውን መወጣት እንዳይችል ያደርጋል። ስለሆነም ሙስናን ለመግታት አለመቻል ወይም አለመፈለግ የዜጎችን የሲቪል፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ሰብአዊ መብቶች  መከበርን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ የመንግስት ውድቀት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ስለዚህ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚደረገው የፀረ-ሙስና ትግል የሰብአዊ መብትን መሰረት ያደረገ የልማት አካሄድ ዋና አካል ተደርጎ ይወሰዳል (UNDP, 2004)።

እንደ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል እ.ኤ.አ. የ2013 ግሎባል ሙስና ባሮሜትር መሠረት፣ በዓለም ዙሪያ 27 በመቶ የሚሆኑ ምላሽ ሰጪዎች ከሕዝብ አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር በሚገናኙበት ወቅት ሙስና አጋጥሟቸዋል (Transparency International, 2013)። ይህ በዋነኛነት የተገለሉ እና ተጋላጭ ቡድኖችን ይጎዳል - የተሻለ የኢኮኖሚ ደረጃ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በመንግስት እርዳታ ላይ ጥገኛ ስላልሆኑ። በመሆኑም ሙስና የህዝብ አገልግሎቶችን ክፍፍል ያዳክማል፣ የፖሊሲ ውሳኔዎችን ከህዝብ ጥቅም ውጭ ያዛባል፣ የህዝብ ሀብት በውጪ እና በመንግስት መዋቅር ውስጥ ባሉ ሙሰኞች እጅ እንዲገባ ያደርጋል (OECD, 2017)። የህዝብ አገልግሎቶችን ጥራት እና መጠን በማዳከም ይህ ዓይነቱ ሙስና ዜጎች በመንግስት ተቋማት ላይ ያላቸውን እምነት በእጅጉ ይጎዳል (Clausen, Kraay and Nyiri, 2010)።

ሙስና የአገልግሎት ጥራትን በተለያዩ መንገዶች ይጎዳል። አቅራቢዎች የተጭበረበሩ ወይም ዝቅተኛ ደረጃ ግብአቶችን በመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ወይም አስፈላጊ አቅርቦቶች ላይ በመጠቀም በታለመላቸው ተጠቃሚዎች ኪሳራ የትርፍ ህዳጋቸውን (profit margin) ሊያሳድጉ ይችላሉ። ጉቦና ምዝበራ የአገልግሎቶች ዋጋን ለአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በማናር ድሆች ማግኘት የሚገባቸውን ቁልፍ መሰረታዊ አገልግሎቶች በአግባቡ እንዳይጠቀሙ ያደርጋል (Kaufmann, Montoriol-Garriga and Recanatini, 2008)።

## ክፍል ሶስት፡- የጥናቱ ስነ-ዘዴ

### 3.1. የጥናቱ ወሰን (Scope of the study)

ይህ ጥናት የተካሄደው በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የአስተዳደር ዘርፍ ስር በሚገኙ ከላይ በክፍል ሁለት በተገለጹት ተቋማት ላይ ነው።

### 3.2. የዝግጅት ምዕራፍ

በመጀመሪያ ለሙስና ሥጋት ሊሆኑ የሚችሉ 10 የትኩረት ርእሰ-ጉዳዮችን በመለየት የመረጃ መሰብሰቢያ ቼክ-ሊስት ተዘጋጅቷል፡፡ እነዚህ 10 ርእሰ-ጉዳዮች ማንኛውም የመንግስት ተቋም ሊተገብራቸው የሚገቡና ተመሳሳይ ባሕሪ ያላቸው አሰራሮች ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው ተቋማት ከተቋቋሙበት ዐላማ አንፃር የራሳቸው የሆነ ልዩ ባሕሪ አላቸው፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ ከተቋማቱ ልዩ ባሕሪ ሊመነጩ የሚችሉና የመለያየት ሁኔታ የሚስተዋልባቸውን የሙስና ስጋቶች ለመለየት አንድ ተጨማሪ ርእሰ-ጉዳይ ተካቷል፡፡

በመቀጠልም በተዘጋጀው ቼክ-ሊስት ዙርያ ለጥናት ቡድን አባላት (መረጃ ሰብሳቢዎች) ስልጠና በመስጠት ወደ መረጃ መሰብሰብ ስራ ተገብቷል፡፡ የተሰጡት ስልጠናዎች ተጨባጭ የሠነድ ፍተሻ በማደረግ መረጃዎችን እንዴት መሰብሰብ እንደሚቻል ለጥናት ቡድን አባላት ግንዛቤ ፈጥረዋል፡፡

### 3.3. የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ቼክ-ሊስት (የዳሰሳ መጠይቅ) እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች (brainstorming) ናቸው፡፡ ከየተቋማቱ የተሰበሰቡ የተለያዩ ሰነዶች ለሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

**ቼክ-ሊስት**፡- የጥናት ቡድን አባላት የተቋማት የተለያዩ የሥራ ክፍል ኃላፊዎችንና ሰራተኞችን በማወያየት እንዲሁም (እንዳስፈላጊነቱ) በምልከታ የተዘጋጀውን ቼክ-ሊስት እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ይህን ጥናት ከሌሎች ለየት የሚያደርገው በቼክ-ሊስት ላይ የተነሱ ነጥቦች አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጣቸው በሰነድ ወይም በምልከታ ሲረጋገጡ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የሙስና ግንዛቤ (perception) ጥናት ሳይሆን በተጨባጭ መረጃ የተቋማት የስራ አፈፃፀም ግምገማ ላይ የተሞረከዘ የሙስና ተጋላጭነት ጥናት ነው፡፡

**ሰነዶች**፡- የተቋማቱ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ የውስጥና የውጪ ኦዲት ሪፖርቶች፣ ዓመታዊ በጀት ዕቅድ፣ የግዥ አፈጻጸም፣ ዓመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የሙስና መከላከል ሠነዶች፣ የጥቆማ ሪፖርት አያያዝ፣ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሪፖርቶች፣ ወዘተ ተዳሰዋል፡፡

**የሃሳብ ማጎልበቻ ዉይይት**፡- ከ10ሩ ርዕሰ-ጉዳዮች ጋር ታያያዥነት ያላቸውን ወይም በቀጥታ በቼክ-ሊስት ውስጥ ያላተካተቱትን የሙስና ስጋቶች በጥቂቱ ለመዳሰስ የበርካታ አመታት ዕውቀት ካላቸው በጥንቃቄ ከተመረጡ ሃላፊዎች እና ባለሙያዎች (experts) ጋር ሃሳብ የማጎልበት ውይይት ተካሂዷል፡፡

### 3.4. የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ

የዚህ ጥናት አቀራረብ በአብዛኛው ዓይነታዊ (qualitative) ነው፡፡ ገላጭ ትንተና (descriptive analysis) አሀዛዊ መረጃዎችን (የፕሮጀክቶች የወጪ መረጃና አፈፃፀም፣ የግዥ አፈፃፀም ማሳያዎች፣ የውጭ እና የውስጥ የኦዲት ሪፖርት ግኝቶች፣ ወዘተ) ለመተንተን ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ከተለያዩ ምንጮች (ቼክ-ሊስት፣ ሰነዶች እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች) የተሰበሰቡ ዓይነታዊ መረጃዎችን ለመተንተን ይህ ጥናት በሰፊው ተቀባይነት ያለውን የጭብጥ ትንተና (thematic analysis) ተጠቅሟል፡፡ በዳሰሳ ጥናቱ ቡድን መሪዎች አስተባባሪነት የጥናት ቡድን አባላት ከየተቋማቱ የተሰበሰቡትን ጥሬ መረጃዎች በዘርፍ ደረጃ በማጠቃለል ትንተና አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ አማካሪዎች በበኩላቸው የሙስና ስጋቶችን በመለየትና በመተንተን ዘርፍ-ተኮር የሙስና መከላከል ምክረ-ሀሳቦችን አስቀምጠዋል፡፡

### 3.5. የጥናቱ ተግዳሮቶች (Challenges of the study)

ጥናቱ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግዳሮቶች አጋጥመውታል፡-

- መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት የተወሰኑ የተቋማት ኃላፊዎች/ባለሙያዎች ቀጠሮ አለማክበር እና የጥናት ቡድን አባላትን ማመላለስ፣
- በአንዳንድ ተቋማት የሚፈለገውን መረጃ በወቅቱ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆንና መረጃ መከልከል፤

### 3.6. የጥናቱ ውስንነቶች (Limitations of the study)

ይህ የዳሰሳ ጥናት ቀድሞ በተመረጡና ለሁሉም ተቋማት ተመሳሳይ በሆኑ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ በማተኮር የተሰራ ከመሆኑ አንፃር የዘርፉን የሙስና ስጋቶች ሙሉ ለሙሉ ለይቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡ በሌላ አገላለፅ በዚህ ጥናት ያልተለዩ ሌሎች የሙስና ስጋቶች በዘርፉ ውስጥ እንዳሉ ይታመናል፡፡ ሆኖም ግን በቀጣይ ለሚሰሩ ጥልቅ ጥናቶች እንደ መንደርደሪያ ሆኖ እንደሚያገለግል መናገር ይቻላል፡፡

## ክፍል አራት፡- ዘርፍ-ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና

በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የአስተዳደር ዘርፍ ስር 18 ተቋማት የተካተቱ ሲሆን የሙስና ስጋት ትንተና መረጃ በተሰበሰበባቸው 11 ርዕሰ-ጉዳዮች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 4.1. የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት

የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የቅንነት፣ ታማኝነት፣ ገለልተኝነት፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ዋና እሴቶች ላይ የተመሰረተ ሥነምግባራዊ ድርጅታዊ ባህልን ለማጎልበት ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ክፍሎቹ ከተሰጣቸው ኃላፊነቶች መካከል፣ የክልል እና የፌደራል ህጎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የተቋሙን የሥነምግባር ፖሊሲዎች መገምገም እና ማዘመን፣ በተቋሙ ውስጥ ካሉ የስነምግባር ጉዳዮች ጋር በተያያዙ የህግ መስፈርቶች ላይ ከፍተኛ አመራሮችን ማማከር፣ ለአመራር እና

ሰራተኞች በሥነምግባር ደረጃዎች (ethical standards) ላይ የሥልጠና ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት እና መተግበር እንዲሁም የሰራተኞች የሥነምግባር ጉድለትን በተመለከተ የሚነሱ ቅሬታዎችን መገምገም እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን መምከር ይገኙበታል። የሥነምግባር ክፍሎች እነዚህን ኃላፊነቶች ለመወጣት በሰው ኃይል፣ በበጀት፣ በቁሳቁስ፣ ወዘተ መሟላት ይኖርባቸዋል። ይህን ታሳቢ በማድረግ የዘርፉ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አደረጃጀት እንደሚከተለው ተተንትኗል።

የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀትን በተመለከተ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የአስተዳደር ዘርፍ ስር ከሚገኙ 18 ተቋማት መካከል በ16ቱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ተደራጅቷል። በዘርፉ ስር የሚገኙት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፣ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ፣ ብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን፣ ቤተመንግስት አስተዳደር፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የግል ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር እና የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር በተፈቀደው የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የስራ መደብ መሰረት ክፍሉን ሙሉ ለሙሉ በሰው ኃይል እንዳሟሉ ከቅጥር ደብዳቤዎች እና ከተደረገ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል። በአንፃሩ የአፍሪካ አመራር ልዕቀት አካዳሚ፣ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ባለስልጣን፣ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ስራ አመራር እና የፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ለክፍሉ አንድ ባለሙያ ብቻ ሲመድቡ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ከተፈቀደው የስራ መደብ ውስጥ 100 በመቶ አላሟሉም። በተጨማሪም በፌደራል የስነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን የስነምግባር መከታተያ ክፍል አንድ ስራ አስፈፃሚ እና አንድ ባለሙያ በተጠባባቂነት እንዲሁም አንድ ባለሙያ በቋሚነት የተመደቡ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።

ከአንድ ተቋም በስተቀር (የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት) አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች የተሟላ መሆኑ በቢሮ ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል። 16ቱ ተቋማት በስራ ክፍሉ የጸደቀ የስራ ዕቅድ አዘጋጅተው ወደ ሥራ የገቡ ሲሆን ሁለቱ ተቋማት (የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት እና የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን) የሥራ እቅድ ስለመዘጋጀቱ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም። በተቋም የሃብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተፈጠሩ አደረጃጀቶችን በሚመለከት በዘርፉ ካሉ 17 ተቋማት ውስጥ 15ቱ አስፈላጊ አደረጃጀቶች ያሏቸው ሲሆን በመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት እና ብሔራዊ የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ስለመኖራቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም።

ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ የአሠራር ሥርዓት መኖሩን በተመለከት በዘርፉ ሥር ከሚገኙ 18 ተቋማት መካከል 17ቱ ተግባራዊ ማድረጋቸዉ በምልከታ የተረጋገጠ ሲሆን የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ግን ይህን ስርዓት ስለመዘርጋቱ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም። ሙስናና ብልሹ አሰራርን በጋር ለመከላከል እንዲቻል የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ ከሌሎች ክፍሎች ጋር በቅንጅት መሥራትን በተመለከተ 11ዱ በቅንጅት የሚሠሩ መሆናቸውን በሰነድ ማስረጃ ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን 6ቱ

(የፌዴራል ፖሊስ ኪሚሽን፣ ብሔራዊ ባንክ፣ የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣ የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት፣ የኢትዮጵያ ኮሙዩኒኬሽን ባለስልጣን እና የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን) በቅንጅት የሚሰሩ ስለመሆናቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

ተቋማትና ግለሰቦች በዘርፉ ሥር ከሚገኙ ተቋማት ጋር በሚያደርጓቸው የሥራ መስተጋበር ውሎች ከመፈረማቸው በፊት በተቋሙ የሕግ ክፍል ተገቢው አስተያየት የሚሠጥበት መሆኑን በተመለከተ በ8ቱ በሕግ የሥራ ክፍል አስተያየት የሚሰጥ መሆኑ በምልከታና ከቀረበ ሰነድ ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፤ በ10ሩ ተቋማት (ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ ቤተመንግስት አስተዳደር፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣ የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት፣ ብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፣ የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ፣ የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት፣ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት እና የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን) ግን ተገቢው አስተያየት የሚሠጥበት ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- የበርካታ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የስራ መደቦች በሰው ኃይል አልተሟሉም፡፡ ይህም ተገቢውን የሙስና ስጋት ግምገማ በማካሄድ አደጋን መሰረት ያደረገ የሙስና መከላከል ስልት ለመንደፍና የቁጥጥር ስርአትን ለማዳበር የሚያስችል አደረጃጀት እንደሌላቸው ጠቋሚ ነው፡፡ በተለይ በሁለት ተቋማት ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አለመደራጀቱ አመራሩ ሥነምግባርን በማስረፅ ረገድ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በቸልተኝነት ወደጎን እንደተወ አመላካች ነው፡፡
- በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው ከሌሎች ክፍሎች ጋር በቅንጅት ስለመስራታቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ ይህ ግኝት ቅንጅታዊ አሰራር መደበኛ እና የተዋቀረ (structured) የሙስናና ብልሹ አሰራር መረጃ ልውውጥ ለማድረግ፣ የጋራ ትንተና ለማካሄድ እንዲሁም የሙስና መከላከል ስትራተጂ ለመንደፍ ካለው ፋይዳ አንፃር የዘርፉ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን አለማድረጋቸውን አመላካች ነው፡፡
- ከግማሽ በላይ በሚሆኑ የዘርፉ ተቋማት ውሎች ከመፈረማቸው በፊት በህግ ክፍል አስተያየት የሚሰጥበት አሰራር ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ አለመደረጉ የመንግስትን ጥቅም ሊጎዱ የሚችሉ ውሎች በሙስና ድርድር/ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው፡፡

## 4.2. ተጠያቂነትን ማስፈን

የተጠያቂነት ስርአት የተቋማት ሀላፊዎች እና ሰራተኞች ለድርጊታቸው፣ ለባህሪያቸው፣ ለአፈፃፀማቸው እና ለሚወስዷቸው ውሳኔዎች ኃላፊነት የሚወስዱበት የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው። የዚህ ስርአት በአግባቡ ተግባር ላይ መዋል ማንኛውም አመራር/ሰራተኛ ከተሰጠው ስልጣንና ከተጣለበት ኃላፊነት አንፃር በአፈፃፀሙ፣ በውሳኔውና በሚያስከትላቸው ተፅዕኖዎች እንደሚገመገም እንዲሁም ብልሹ አሰራሮች መኖራቸው ከተረጋገጠ አንደአስፈላጊነቱ የእርምት እርምጃዎች እንደሚወሰዱ ማረጋገጫ ይሰጣል። ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ተጠያቂነትን ከማስፈን ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

በጠቅላይ ሚኒስቴር ዘርፍ ስር ከሚገኙት ተቋማት መካከል ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎችን አሰራር በተመለከተ የሙስና ስጋት ጥናት ያካሄዱት ስድስቱ ብቻ (የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ የግል ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ አርቴፊሻል ኢንተለጀስ ኢንስቲትዩት፣ ብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር እና የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት) ሲሆኑ፤ ሌሎቹ ጥናት ስለማከናወናቸው መረጃ አልቀረበም። ከዚህ ጋር በተያያዘ ጥናቱን ተመርኩዞ አሠራራቸውን የማሻሻልና የማረም ሥራ የሰሩት ሶስት ተቋማት ብቻ ናቸው (የግል ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር እና አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት)።

በዘርፉ ስር ካሉ ተቋማት መካከል የደንበኞች እርካታን በየጊዜው በገለልተኛ አካል ያስጠኑት ብሔራዊ ባንክ እና የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ተቋማት ይህን ማከናወናቸውን የሚገልፅ መረጃ አልቀረበም። በተጨማሪም 13 የዘርፉ ተቋማት የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) ያዘጋጁ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ አምስቱ (የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣ ብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን፣ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት እና የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን) ስለማዘጋጀታቸው መረጃ አልቀረበም።

የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ ቅድመ-መከላከል ሥራዎችን የሠሩት አምስት ተቋማት ብቻ (ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ የግል ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን) ሲሆኑ፤ በሌሎች 13ቱ ላይ የቅድመ መከላከል ሥራ ስለመሠራቱ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም። በሶስት ተቋማት ውስጥ በሥነምግባር ጉድለት ምክንያት ስድስት ኃላፊዎች ላይ ክስ የተመሠረተ ሲሆን፤ አራቱ ላይ ውሳኔ ተላልፏል። በተመሳሳይም በአምስት ተቋማት ውስጥ 41 ባለሙያዎች በሥነ-ምግባር ጉድለት ተከስሰው በ39ኙ ላይ ውሳኔ የተላለፈ መሆኑን የቀረቡ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በስምንት ተቋማት የሚገኙ የሕግ ክፍሎች ከተመሠረቱት ክሶች ውስጥ 80% በላይ አሸናፊ መሆናቸውን፣ እንዲሁም በሰባት ተቋማት ውስጥ ከቀረቡ 379 ቅሬታዎች መካከል 306 ምላሽ ያገኙ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ክፍልን ከማገዝና ከመደገፍ አንጻር በዘርፉ ካሉ 18 ተቋማት መካከል የዘጠኝ ተቋማት የበላይ ኃላፊዎች (የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ የግል ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የአፍሪካ የአመራር ልህቀት አካዳሚ፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር እና የኢፌድሪ ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት) የክፍሉን የሥራ ክንውን ግምገማ የሚያደርጉ ሲሆን የሌሎቹ ተቋማት ኃላፊዎች ግምገማ ስለማድረጋቸው መረጃ አልቀረበም፡፡

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- በዘርፉ ስር የሚገኙ አብዛኛው ተቋማት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎች አሰራር ላይ የሙስና ስጋት ጥናት አለማካሄዳቸው፣ እንዲሁም ሁሉም ተቋማት በሚያስብል ደረጃ የደንበኞች እርካታን በየጊዜው በገለልተኛ አካል አለማስጠናታቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ እነኚህ ተግባራት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጡ የሚችሉ አሰራሮችን በጥናት በመለየት ቅድመ-መከላከል ስትራተጂዎችን ለመቅረፅ እንዲሁም ተጠያቂነትን ለማስፈን ካላቸው ፋይዳ አንፃር ተቋማቱ የሚጠበቅባቸውን አለማድረጋቸውን ያሳያል፡፡
- በዘርፉ ስር የሚገኙ አምስት ተቋማት የሥነምግባር ደንብ ስለማዘጋጀታቸው የሚያመላክት መረጃ አልተገኘም፡፡ የሥነምግባር ደንብ አለመኖር የተቋማቱን እሴቶች፣ ደንቦች፣ ደረጃዎች እና መርሆዎች በተመለከተ አመራርና ሠራተኞች በቂ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው በማድረግ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን መሰረት አድርጎ ሥራን ከመስራት አኳያ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡
- በዘርፉ ስር የሚገኙ ሁለት-ሶስተኛው ተቋማት የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ የተደረጉ ቅድመ-መከላከል ስራዎችን የሚያሳይ መረጃ አላቀረቡም፡፡ በመሆኑም የሙስና ስጋቶች አድገው ወደ ሙስና ከመሸጋገራቸው በፊት በመረጃዎች ላይ በመመስረት የሚወሰድ የእርምት እርምጃ አለመኖር ለሃብት ብክነትና ለደንበኞች እንግልት ሊዳርግ ይችላል፡፡
- በገሚሱ የዘርፉ ተቋማት የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ ክንውን በበላይ አመራሮች ክትትልና ግምገማ እንደሚደረግበት የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ይህም የተቋማት አመራሮች በተቋማቸው ለሚካሄድ የፀረ-ሙስና ትግል የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ከማድረግ አንፃር በቂ ትኩርት አለመስጠታቸውን የሚያሳይ ክፍተት ነው፡፡

## 4.3. የተቋማት ግልፅነት

የመንግስት ተቋማት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ግልፅነትን ሊላበሱ ይገባል፡፡ ግልፅነት ዜጎች ለህብረተሰቡ አገልገሎት ለመስጠት የተዋቀሩ ተቋማትን የስራ አፈፃፀም እንዲሁም የሚከሰቱ ችግሮችን መንስኤ እና መዘዞችን በተመለከተ በቂ መረጃ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው፡፡ የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖሊሲዎች እና የውጤቶች አተገባበር መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያጠቃለለ ነው፡፡ ግልፅነት የጎደለው አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ምንም እንኳን መልካም ውጤት ቢመዘገብም የተአማኒነት እና ቅቡልነት ጥያቄ ሊነሳበት ስለሚችል የሚያሳድረው ተፅእኖ ቀላል አይደለም፡፡ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለውን የግልፅነት ስራዎች በዚህ ክፍል ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ውስጥ እቅዶች እና የእቅድ አፈፃፀሞች በጋራ ውይይት የሚደረግባቸው መሆኑን ከተሰበሰበው መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት መካከል 12ቱ ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ የሚያደርጉ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ስድስት ተቋማት ይህን ማድረጋቸውን የሚገልፅ መረጃ አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም የሥራ ሂደቶች ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚመለከታቸው አካላትን ማሳተፍ በተመለከተ ገሚሱ የዘርፉ ተቋማት የሚያሳትፉ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ ግን ማሳተፋቸውን አመላካች ሰነድ አልተገኘም፡፡ በዘርፉ ስር ከሚገኙ ተቋማት ስምንቱ ውሳኔዎች እና ቃለ-ጉባኤዎችን በተገቢው መንገድ ተደራሽ ሲያደርጉ ቀሪዎቹ መረጃዎችን ተደራሽ እንደሚያደርጉ አመላካች ሰነድ አልቀረበም፡፡

የግዥና ጨረታ ማስታወቂያዎችን በተለያዩ ሚዲያዎች (ጋዜጣ፤ ሬድዮ፤ ቴሌቭዥን፣ ወዘተ) በይፋ ማሰራጨትን በተመለከተ 15ቱ የዘርፉ ተቋማት የሚያሰራጩ መሆኑ በመረጃ ሲረጋገጥ፤ ቤተመንግስት አስተዳደር፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና ብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ግን ይህን ስለማድረጋቸው የሚገልፅ መረጃ አልቀረበም፡፡ ዘጠኝ የዘርፉ ተቋማት ግልጽነትን ከማጉላት አንፃር መረጃ ለሚዲያ፣ ለምርመራ ጋዜጠኖች እና ለሌሎች አካላት የሰጡ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ መረጃ ስለመስጠታቸው የሚያመላክት ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ በስተቀር 17ቱ ተቋማት የራሳቸውን መረጃዎች የሚያሰራጩበት ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ድረ-ገጽ ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- ገሚሱ የዘርፉ ተቋማት በስራ ሂደቶች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የሚመለከታቸው አካላት እንደሚሳተፉ መረጃ አላቀረቡም፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ውሳኔዎች እና ቃለጉባዔዎች

ተደራሽ ስለመደረጋቸው የሚያሳይ መረጃ በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት አልቀረበም። ይህም ግልፅነትን ከማስፈን አኳያ በዘርፉ ውስጥ ክፍተቶች እንዳሉ ያሳያል።

- ግልፅ የበጀት ሂደትና አጠቃቀም መረጃ የሕዝብ አመለካከት እና ጥቅም እንደሚከበር እንዲሁም የመንግስት ገንዘብ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንደሚውል በህብረተሰቡ ዘንድ እምነትን ያሳድራል። ስለሆነም ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ የሚደረግበት አሰራር አለመኖሩ ተቋማቱ የተመደበላቸውን ሃብት በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋላቸውን በተመለከተ ጥያቄ የሚያስነሳ የግልፅነት ክፍተት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።
- ለመገናኛ ብዙሃን ተደራሽ መሆን ላይ ያሉ ውስንነቶች መረጃዎች ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዳይሆኑ እንዲሁም አጠቃላይ የሚሰጡ አገልግሎቶች ለህዝብ ግልጽ እንዳይሆኑ በማድረግ ያለክፍያ ለሚሰጡ መደበኛ የተቋማት አገልግሎቶች ተገልጋዮችን ተገቢ ያልሆነ ክፍያ ለመጠየቅ (ተገልጋዮች መብታቸውን በገንዘብ እንዲገዙ) በር የሚከፍት የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

## 4.4. አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

ሙስናን ለመዋጋት ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሚናቸው ከፍተኛ ነው። የህግ የበላይነት ከማስፈን ባሻገር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸውን መርሆች በመደንገግ ፈፃሚዎች ስራቸውን ህግን በተከተለ መሰረት እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታን ይፈጥራል። አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው መሻሻል ይኖርባቸዋል። ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ከአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ተያይዘው የተሰሩ ስራዎችን ከዚህ በታች ለመተንተን ተሞክሯል።

ጥናቶችን እና የዕለት-ተለት ሥራዎችን መሠረት በማድረግ ደንቦች እና መመሪያዎች የመለየትና የማሻሻል ሥራዎችን በተመለከተ 10 ተቋማት በድምሩ 33 ለፀረ-ሙስና አዋጁ ደጋፊ የሆኑ ሰነዶች፣ ስምንት አዲስ የወጡ ደንቦች፣ 68 የተሻሻሉ መመሪያዎች ያዘጋጁ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ 25ቱ በፍትህ ሚኒስቴር የተመዘገቡ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ቀሪዎቹ ተቋማት ደንብና መመሪያዎችን ስለማሻሻላቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም። ለአመራሮች እና ሰራተኞች በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች አተገባበር ላይ 12 ተቋማት ሥልጠና የሰጡ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ተቋማት ግን ይህን ስለማከናወናቸው መረጃ አላቀረቡም። ገሚሱ የዘርፉ ተቋማት ፀድቀው የሚወጡ መመሪያዎችን ለተገልጋዮች/ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ ማድረጋቸውን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል። ቀሪዎቹ ተቋማት ግን ተደራሽ ስለማድረጋቸው መረጃ አልቀረበም።

የዜጎች ቻርተርን (የደንበኛ አገልግሎት ስታንዳርድ) በተመለከተ ስምንት ተቋማት ያዘጋጁ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ተቋማት (ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ ብሔራዊ ባንክ፣ የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ

ዋስትና አስተዳደር፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣ የአፍካ አመራር ልህቀት አካዳሚ እና የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት) ቻርተሩን ስለማዘጋጀታቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ የዜጎች ቻርተር ከአዘጋጁት ተቋማት ውስጥ የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የአፍካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ለተገልጋዮቻቸው ተደራሽ ማድረጋቸውን በአመላካች ሰነዶች/ምልከታዎች የተረጋገጠ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ተደራሽ ስለማድረጋቸው መረጃ አልቀረበም፡፡

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- ከግማሽ በላይ በሚሆኑት የዘርፉ ተቋማት የዜጎች ቻርተር ስለመዘጋጀቱ መረጃ አልቀረበም፡፡ ቻርተሩን ካዘጋጁትም ውስጥ የተወሰኑት በተገቢው መንገድ ለተገልጋዮች ተደራሽ አላደረጉም፡፡ በተጨማሪም ገሚሱ የዘርፉ ተቋማት ፀድቀው የሚወጡ መመሪያዎችን ለተገልጋዮች/ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ ማድረጋቸውን የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ ይህ ክፍተት ተገልጋዮች ባለማወቅ መብታቸውን በገንዘብ እንዲገዙ እንዲሁም የተቋማቱ አሠራር ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዳይኖረው ሊያደርግ ስለሚችል የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡
- ሲሶው የዘርፉ ተቋማት ውስጥ ለአመራርና ሰራተኞች በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ አተገባበር ላይ ስልጠና ስለመሰጠቱ መረጃ አልቀረበም፡፡ ይህ ጉድለት በሠራተኞች የሥራ አፈፃፀም ላይ ከሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ በተጨማሪ ሠራተኞች ከዕውቀት ክፍተት ጋር ተያይዞ ለብልሹ አሠራር እንዲጋለጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- ወደግማሽ የሚጠጉት የዘርፉ ተቋማት ጥናቶችን መሰረት በማድረግ አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ ስለማከናወናቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ በየጊዜው እየተራቀቁ የመጡት የሙስና ስልቶች ነባር ህጎች ያለባቸውን ክፍተት በመጠቀም የሚሰሩ ከመሆናቸው አንፃር ህጎቹን የመፈተሽና የማሻሻል ተግባር እንደመደበኛ የተቋማት የስራ አካል ተወስዶ አለመሰራቱ ለሙስና መከላከል ተገቢ ትኩረት እንዳልተሰጠ አመላካች ነው፡፡

## 4.5. የንብረት አስተዳደር

የንብረት አስተዳደር ስርአት ውጤታማነት የሚለካው ከንብረት ርክክብ እስከ ማስወገድ ድረስ በየደረጃው የሚከናወኑ ተግባራትን በአግባቡ በመተግበር ንብረቱ በአግባቡ ተጠብቆ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ሲቻል ነው፡፡ ንብረትን ከማስተዳደር አኳያ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የተገዙ ንብረቶችን መረከብ፣ በተገቢው መንገድ ማከማቸትና መጠበቅ፣ ለተጠቃሚዎች ማድረስና ንብረቶቹ ለተገቢው አገልግሎት መዋላቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ያለአገልግሎት የተቀመጡትን (ወይም የአገልግሎት ጊዜያቸውን ያጨረሱትን) የንብረት አስተዳደር መመሪያን በተከተለ መልኩ ማስወገድ ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በየጊዜው የንብረት ቆጠራ በማካሄድ የማረጋገጥ ስራ

መስራት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ካለው የንብረት አስተዳደር ስርአት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በዘርፉ ሥር በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ንብረት የማስተዳደርና የመቆጣጠር አሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዘርፉ ሥር ባሉ 17 ተቋማት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እንደሚደረግ ከተሰበሰቡ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡ በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ግን ዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

ንብረት አወጋገድን በተመለከተ በ11 የዘርፉ ተቋማት በ2013 እና 2014 የበጀት ዓመት ቴክኖሎጂ ያለፈባቸው ግምታቸው ብር 32,136,607.00 የሆነ እና የመጠቀሚያ ጊዜአቸው ያለፈባቸው ግምታዊ ዋጋቸው ብር 5,295,256.00 የሆነ ንብረቶች የተወገዱ መሆኑን ከተሰበሰበው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ግምታቸው ብር 25,914,407.00 የሆኑት ንብረቶች በግልጽ ጨረታ ሲወገዱ፣ የቀሩት ደግሞ በውስን ጨረታ እና በእርዳታ/ስጦታ የተወገዱ መሆኑ ታውቋል፡፡ በዘርፉ ስር ባሉ 15 ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝር ቀርቦ በባለሙያዎች መገምገሙ ሲታወቅ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት እና የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን ግን ይህን ስለማከናወናቸው መረጃ አልተገኘም፡፡

የሚወገዱ ንብረቶችን ተገቢ ጥበቃ እና አያያዝ በተመለከተ በዘርፉ በሚገኙ 14 ተቋማት ተገቢ ጥበቃ እንደሚደረግ በምልከታ ሲረጋገጥ፣ በአራት ተቋማት (የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት፣ ብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን እና የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን) ግን በምልከታ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ሥር ከሚገኙ 18 ተቋማት መካከል በስምንቱ የካይዘን ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፤ በቀሪዎቹ ተቋማት ላይ ስለመተግበሩ የሚሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- በሶስት ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝራቸው ቀርቦ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተገምግመው የሚወገዱ መሆናቸውን የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ የግምገማ አለመኖር ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ንብረቶች በሙስና ድርድር እንደአላስፈላጊ ወይም ጊዜ ያለፈባቸው ተፈርጀው ሊወገዱ የሚችሉበትን አጋጣሚ ሊፈጥር ስለሚችል የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡
- የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርዓትን የተገበሩት ከግማሽ በታች የዘርፉ ተቋማት ብቻ መሆናቸውን በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ ስርአት አለመተግበሩ እቃዎች በበቂ መጠን በመጋዘን ባሉበት ሁኔታ ተጨማሪ ግዥዎችን በማከናወን የህዝብን ሃብት ለብልሽት እና ብክነት ሊያጋልጥ ከመቻሉ በተጨማሪ እጥረት ያለባቸውን ግብአቶች በወቅቱ መለየት ካለመቻል የተነሳ አስፈላጊ አገልግሎቶች የሚቋረጡበትን ሁኔታ በመፍጠር ተገልጋዮችን ለእንግልት ሊዳርግ ይችላል፡፡

### 4.6. የግዥ አስተዳደር

ተቋማት ሥራቸውን በሚፈለገው ጊዜና ጥራት ለማከናወን አስፈላጊ የሚባሉ ግብአቶችንና የስራ መሳሪያዎችን ሟሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህን ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የዕቃና የአገልግሎት ግብአቶችና መሳሪያዎች ለሟሟላት የግዥ ስርአትን የተከተለ ስልታዊ አካሄድ ይጠይቃል፡፡ የግዥ ስርአቱ ያለበትን ደረጃ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናቱ እንደሚከተለው ተንትኗል፡፡

ተቋማት በቀጣይ በጀት ዓመት የሚያከናውኗቸውን ግዥዎች አስቀድመው በማቀድ ተገቢ ስለመሆናቸው ግምገማ በማድረግ አፅድቀው በግዥ ሕጉ መሠረት የተፈቀዱ ግዥዎችን እንዲያከናውኑ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ አንፃር በዘርፉ ስር ከሚገኙ ተቋማት መካከል 13ቱ የግዥ እቅድ ላይ ግምገማ የሚያደርጉ መሆኑን መረጃ ሲያቀርቡ፣ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ ቤተመንግስት አስተዳደር፣ ብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን እና የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ግን ይህን ስለማድረጋቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ የግዥ አፈፃፀምን በተመለከተ 11 ተቋማት ግምገማ ያካሄዱ ሲሆን ቀሪዎቹ ሰባት ተቋማት (ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ ቤተመንግስት አስተዳደር፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን እና የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን) ግን የግዥ አፈፃፀም ግምገማ ስለማድረጋቸው መረጃ ያላቀረቡ ናቸው፡፡

የዘርፉን የግዥ አፈጻጸም በሚመለከት ያለ ዕቅድ በሰባት ተቋማት የ175 ሚሊዮን ብር፣ በፕሮፎርማ በ12 ተቋማት የ105 ሚሊዮን ብር፣ በውስን ጨረታ በዘጠኛ ተቋማት የ76.2 ሚሊዮን ብር፣ እንዲሁም በተደጋጋሚ ከአንድ አቅራቢ በሰባት ተቋማት የ81 ሚሊዮን ብር ግዥ በ2014 በጀት ዓመት መፈጸሙን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዘርፉ ተቋማት ቅሬታ የቀረበባቸው እንዲሁም የሙስና ጥርጣሬ ቀርቦባቸው የተሰረዙ ግዥዎች ስለመኖራቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

በዘርፉ ስር ከሚገኙ 18 ተቋማት ውስጥ 12ቱ ግዥ ከመፈጸማቸው በፊት ንብረቶቹ በስቶክ መኖር ወይም አለመኖራቸው የሚረጋጥበት ሥርዓት የዘረጉ ሲሆን፣ ስለቀሪዎቹ ተቋማት ግን መረጃ አልቀረበም፡፡ የገበያ ጥናትን በተመለከተ ገሚሱ የዘርፉ ተቋማት ግዥ ከመፈፀማቸው በፊት የሚያካሂዱ ሲሆን ቀሪዎቹ ግን የገበያ ጥናት ስለማድረጋቸው መረጃ አላቀረቡም፡፡ ከ18 የዘርፉ ተቋማት መካከል ሰባቱ ዲጂታላይዝድ የግዢ ሥርአት የሚጠቀሙ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ቀሪዎቹ ግን ይህን ስርአት 11 ስለመጠቀማቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- ወደ ሁለት-ሶስተኛ የሚጠጉ የዘርፉ ተቋማት ዲጂታላይዝድ የግዢ ስርአት እንዳልተገበሩ ታውቋል። የተለመደው የማንዋል ግዥ ስርአት በተደጋጋሚ አካላዊ ግንኙነት የታጀበ ከመሆኑ አንፃር ለሙስና ድርድር ሊጋብዝ ይችላል።
- ሲሶው የዘርፉ ተቋማት ግዥ ከመፈጸማቸው በፊት ንብረቶቹ በስቶክ መኖር ወይም አለመኖራቸው የሚረጋጥበትን ሥርዓት የዘረጉ ስለመሆኑ መረጃ አልቀረበም። ይህ ክፍተት በቂ ስቶክ ባለበት ሁኔታ ተጨማሪ ግዥዎችን በማከናወን የህዝብን ሃብት ለብልሽት እና ብክነት ሊዳርግ ይችላል።
- በገሚሱ የዘርፉ ተቋማት ውስጥ ግዥ ሲከናወን በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ ለተጋነነ የምርቶች/አገልግሎቶች ዋጋ ስለሚጋብዝ የሙስና ስጋት ነው።
- የተወሰኑ የዘርፉ ተቋማት የግዥ ዕቅድ እንዲሁም የግዥ ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ግምግማ እንደሚያከናውኑ በማስረጃ ሊረጋገጥ አልቻለም። ይህም ግልፅነት እና ተጠያቂነትን ከማስፈን አኳያ በዘርፉ ውስጥ እጅግ አሳሳቢ የሆኑ ክፍተቶች እንዳሉ ያሳያል።
- በዘርፉ ተቋማት በርካታ ሚሊዮን ብሮች ግምት ያላቸው የፐሮፎርማ ግዢዎች፣ የውስን ጨረታ ግዢዎች፣ ከአንድ አቅራቢ ተደጋጋሚ ግዥዎች እና ያለዕቅድ ግዥዎች መከናወናቸው የግዥ ዕቅዶች ክፍተት እንዳለባቸው አመላካች ከመሆናቸው ባሻገር የዘርፉ የግዥ ስርዓት የሙስና ስጋት እንዳለበት አመላካች ናቸው (እነኚህ ግዢዎች እንዲካሄዱ የሚያስገድድ ህጋዊ መሰረት ሊኖር የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ)።

## 4.7. የሰው ሃብት አስተዳደር

የአንድን ተቋም ስኬት ከሚወስኑ መስረታዊ ግብኣቶች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ያላቸው የሰው ሃብት ነው። ስኬት የሚረጋገጠው የሰው ሃብት በአግባቡ ማስተዳደር ሲቻል ነው። ለዚህ የሚያግዙ አሰራሮችና መዋቅሮች መዘርጋት ተገቢነቱ የጎላ ነው። ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የሰው ሃብት አስተዳደር ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል።

የሰው ሃብት አስተዳደርን በሚመለከት በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በስተቀር ሁሉም በሰራተኛ አስተዳደር ክፍል የተለያዩ ኮሚቴዎች የተደራጁ መሆኑን የሚያመላክቱ መረጃዎች ቀርበዋል። ከግል ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር እና አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት በስተቀር በተቀሩት የዘርፉ ተቋማት የቅጥር ማስታወቂያዎች ለሁሉም ተደራሽ እንደሚደረጉ ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ተችሏል።

በአራት የዘርፉ ተቋማት የሰራተኛ አስተዳደር አሠራሮች ላይ በ2013 እና 2014 የበጀት ዓመት ቅሬታዎች የቀረቡ ሲሆን ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ቅሬታዎቹ ተፈተዋል፡፡ ቀሪዎቹ 14 ተቋማት ላይ ቅሬታ ስለመቅረቡ መረጃ አልቀረበም፡፡

በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ቁጥራቸው 2309 በሆኑ ሠራተኞች ላይ የትምህርት ማስረጃና የሥራ ልምድ ሰነድ የማጣራት ስራ አከናውኖ 21 ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ እንዲሁም 31 ሀሰተኛ የሥራ ልምድ ሰነድ ማግኘቱን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተመሳሳይም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በ111፣ የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት በ153 እንዲሁም የኢፌድሪ ፕሬዚደንት ጽ/ቤት በአራት የትምህርት ማስረጃዎች ላይ የማጣራት ስራ ሰርተዋል፡፡ ቀሪዎቹ 14 ተቋማት ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃና የስራ ልምድ የማጣራት ስራ ስለመስራታቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ በመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ በፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (በከፊል)፣ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ በኢትዮጵያ ስራ አመራር እና በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የአመራር ሹመት በውድድር ላይ የተመሰረተ መሆኑን ከተሰበሰቡ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ በቀሪዎቹ 12 ተቋማት የአመራር ሹመት በውድድር ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

ከመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ ከፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት፣ ከግል ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር እና ከፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በስተቀር ቀሪዎቹ 14 ተቋማት የሰው ሃብት አስተዳደር ሥራቸውን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አደራጅተው እንደሚሠሩ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተጨማሪም አስር የዘርፉ ተቋማት በድምሩ ለ5068 ሠልጣኞች የሙያ ብቃት ማጎልበቻ፣ እንዲሁም ለ4930 ሠልጣኞች የሥነ-ምግባር ማሻሻያ ሥልጠናዎች የሰጡ ሲሆን፤ የተቀሩት ግን ይህን ስለማከናወናቸው መረጃ አልቀረበም፡፡

### ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- ሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ ሰነድ የማጣራት ስራ በ14ቱ የዘርፉ ተቋማት እንዳልተከናወነ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ የሰነድ ማጭበርበር እንደ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም አገልግሎቶች ያሉ ጥቅማጥቅሞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ለማግኘት በማሰብ ሆን ተብሎ የሚደረግ አታላይ ድርጊት ከመሆኑ አንፃር የማጣራት ስራ አለመሰራቱ ተቋማቱን ለከፍተኛ የሙስና አደጋ ሊያጋልጣቸው ይችላል፡፡
- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የሰው ሃብት አስተዳደር ስርአት በተወሰኑ የዘርፉ ተቋማት አለመገንባቱ በቅጥር፣ ዝውውር፣ እድገት፣ ወዘተ ውሳኔዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡

- ሙስናን ከውስጥ መከላከል የሚቻለው አመራርና ሰራተኞች የታማኝነት፣ የተጠያቂነት፣ የፍትሃዊነት እና የመተማመን ጠንካራ የሞራል እሴቶችን ካዳበሩ ነው፡፡ የሥነምግባር ስልጠናዎች በዚህ ረገድ ያላቸው አስተዋፆ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት በሥነምግባር ዙሪያ የስልጠናዎች አለመኖር አመራርና ሰራተኞች ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዲፀየፉና እንዲታገሉ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት በሚፈለገው ልክ ከግብ እንዳይደርስ ሊያደርግ የሚችል ክፍተት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

## 4.8. የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ

የሃብት ምዝገባ ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል፣ ተቋማዊ ኃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይጋጩ በራሳቸው መንገድ እንዲመሩ ለማድረግ፣ አላግባብ የተፈራ ምንጩ ያልታወቀ ሃብትን ለማጋለጥ እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ጥልቅ ፋይዳ ያለው ሥርዓት ነው፡፡ ሥርዓቱ በተባበሩት መንግስታት የፀረሙስና ስምምነት፣ በአፍሪካ ህብረት የሙስና መዋጊያ እና መከላከያ ስምምነት እንዲሁም የዓለም አቀፍና የአህጉር አቀፍ የፀረ-ሙስና ስምምነቶችን ተቀብለው በሚፈፅሙ ሀገራት እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም ሥርዓቱን ባለፉት አሥር ዓመታት ስትተገብር ቆይታለች፡፡ ሃብትና የገቢ ምንጫቸውን ማስመዝገብ ካለባቸው አካላት መካከል የፌደራል ተቋማት አመራሮችና ሠራተኞች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በ2013 በጀት ዓመት በዘርፉ ሥር የሚገኙ የሁሉም ተቋማት አመራሮች እና ሰራተኞች ሃብታቸውን በhardcopy እንዳስመዘገቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኖም በሲስተም ሙሉ ለሙሉ ያስመዘገቡ የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና አርቴፍሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ብቻ ናቸው፡፡ በሲስተም ማስመዝገብ እስካሁን ያልጀመሩ ደግሞ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አገልግሎት ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ አፈፃፀማቸው በተለያየ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ በዘርፉ ሥር በሚገኙ ተቋማት በድምሩ 261 አመራሮች እና 6894 ሠራተኞች ሀብታቸውን እንዳስመዘገቡ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## 4.9. የፕሮጀክቶች አስተዳደር

ፕሮጀክቶች ከቅድመ ግንባታ እስከ ፍፃሜቸው ድረስ አግባብነት ያላቸውን ህጎችና መስፈርቶች ተከትለው እየተፈጸሙ ስለመሆናቸው ቴክኒካል ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርግ የተለየ የኦዲት መዋቅር ባለመኖሩ፣ በተለያዩ አካላት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ለጥራት መጓደልና ብክነት እየተጋለጡ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክትን በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ፣ በጀትና የጥራት ደረጃ ለማጠናቀቅ የዲዛይን ጥራት፣ የጨረታ አወጣጥ ሂደት፣ የክፍያ ስርአት፣ የኮንትራት አስተዳደር እና ከመሰል ጉዳዮች ጋር ተያይዞ የተጠናከረ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ያፈልጋል፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የግንባታ ፕሮጀክት አስተዳደር ለሙስና ያለውን ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዘርፉ ስር ከሚገኙ ተቋማት መካከል በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ በመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ በኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ በአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን እና በቤተመንግሥት አስተዳደር ተጀምረው በጊዜያቸው ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች መኖራቸው ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በድምሩ 13 ሚሊዬን ብር የሚሆን የዋጋ ማስተካከያ የተደረገባቸው ፕሮጀክቶች በአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን መኖራቸውን የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የገንዘብ መጠኑ በድምሩ 1.5 ቢሊዬን ብር የሚሆኑ ተጨማሪ ሥራ የተሰጠባቸው በኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት አንድ ፕሮጀክት፣ በቤተመንግስት አስተዳደር 13 ፕሮጀክቶች፣ በአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ አራት ፕሮጀክቶች፣ በመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር አንድ ፕሮጀክት፣ እንዲሁም በአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አንድ ፕሮጅክት (በአጠቃላይ 21 ፕሮጀክቶች) መኖራቸውን የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ ምክንያቶች ውል የተቋረጠባቸው 12 ፕሮጀክቶች በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ውስጥ እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- የፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያለመጠናቀቅ (ይህም ለተጨማሪ ከፍተኛ ወጪ መዳረግ) ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደት መጓተት፣ በአሰሪና ተቋራጭ መካከል ቅንጅት ማነስ፣ በአጠቃላይ ከፕሮጀክቶች አስተዳደር የክትትልና ቁጥጥር መላላት ሊመነጭ የሚችል አሳሳቢ ክፍተት ነው፡፡ በተጨማሪም ያላግባብ ተጨማሪ ወጪ ለመጠየቅ ከተያዘላቸው ቀነገደብ በላይ እንዲሻገሩ ለማድረግ የታለመ ሊሆን ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው፡፡
- የውሎች መቋረጥ እንዲሁም የተቋራጮች መጥፋት መፅደቅ የማይገባቸው ጨረታዎችን ከማፅደቅ ወይም ማሸነፍ የማይገባቸው ተጫራቾች እንዲያሸንፉ ከማደረግ ጋር ተያይዞ የመምጣት ዕድል ሊኖረው ስለሚችል አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡
- ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ የሚሰጥበት አሰራር (Variation work order) ምናልባት ቀድሞ የፕሮጀክቱን ዕቅድ በተገቢው መንገድ ከመገምገምና የሚሰሩ ስራዎች አስቀድመው እንዲካተቱ ከማድረግ አንፃር ክፍተት እንዳለ ጠቋሚ ሊሆን ይችላል (በአገሪቱ ኢኮኖሚ ሁኔታዎች ላይ በተከሰተ ለውጥ ምክንያት የመመጣት እድሉ እንደተጠበቀ ሆኖ)፡፡
- የዋጋ ማስተካከያ በተለያዩ ግንባታዎች ላይ የሚሰጥበት አሰራር ከዕቃዎች የዋጋ መናር አንፃር የመነጨ ሊሆን ቢችልም፣ ከአላግባብ የጥቅም ግንኙነት ጋር ተያይዞ የመምጣት ዕድል ሊኖረው ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

## 4.10. ኦዲትና ቁጥጥር

ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በዘረጉ ተቋማት ለሙስና የሚያጋልጡ ብልሹ አሰራሮችና ሙስና በእጅጉ እንደሚቀንስ የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ተቋማት ህጋዊና ጤናማ

የሆነ የገንዘብና የንብረት አያያዝ እንደተከተሉ ለማረጋገጥ በየጊዜው በውስጥም ሆነ በውጭ ኦዲተር የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሠራራቸውን የማስገምገም ግዴታ አለባቸው፡፡ በዚሁ መሠረት በዘርፉ ሥር በሚገኙ ተቋማት የኦዲት አስተዳደር ስርአት በጥናቱ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

በዘርፉ ስር ባሉ ሁሉም ተቋማት ውስጥ የኦዲት ሥራ እንደሚሠራ የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል፡፡ በኦዲት ግኝቶች ላይ በ15 ተቋማት ውስጥ ውይይት የሚደረግ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት እና የቤተመንግስት አስተዳደር በኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይት ስለማድረጋቸው መረጃ አልቀረበም፡፡

በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ 18 ተቋማት ውስጥ በ14ቱ የኦዲት ግኝትን መሠረት በማድረግ ማሻሻያዎች የሚደረጉ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት፣ የቤተመንግስት አስተዳደር እና የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን በኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይት ስለማካሄዳቸውም ሆነ ማሻሻያዎች ስለማድረጋቸው መረጃ አልቀረበም፡፡

የዘርፉ 11 ተቋማት ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል፣ ለተቋማዊ ለውጥ እና ለሕግ ክፍል የኦዲት ሪፖርቱን ተደራሽ የሚያደርጉ ሲሆን፣ የፐሬዝዳት ጽ/ቤት ደግሞ ከነዚህ የስራ ክፍሎች በተጨማሪ ለመገናኛ ብዙሀን ተደራሽ እንደሚያደርግ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ቀሪዎቹ የብሔራዊ ባንክ፣ የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት፣ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን፣ የአፍሪካ አመራር ልዕቀት አካዳሚ እና የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን የኦዲት ሪፖርት ለተገልጋዮች ተደራሽ ስለማድረጋቸው የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡

በዘረፉ ከተከናወኑ የኦዲት ስራዎች የሚከተሉት ግኝቶች ተጠቃሽ ናቸው፥-፡-

- በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ሳይወራረዱ የቀሩ ሂሳቦች (ለማሳያነት ያህል የወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ ከብር 7.8 ሚሊዬን በላይ) መኖሩ፣
- በአፍሪካ አመራር ልዕቀት አካዳሚ ከብር 72.2 ሚሊዮን በላይ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣ በተጨማሪም ከብር 27.8 ሚሊዮን በላይ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፣
- በአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ከብር 1.9 ቢሊዮን በላይ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣
- በፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከብር 5.6 ሚሊዮን በላይ ያልተወራረደ ሂሳብ እና ከብር 8.4 ሚሊዮን በላይ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፣ በተጨማሪም በድምሩ ከብር 1.06 ሚሊዮን በላይ የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያዎች የተፈፀሙ መሆኑ፣
- በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ከብር 4.5 ሚሊዬን በላይ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት መኖሩ፣

**ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች**

- የኦዲት ግኝቶች ላይ በመመስረት የተወሰዱ ማሻሻያዎች ስለመኖራቸው የሚያሳይ መረጃ ከአራቱ የዘርፉ ተቋማት አልቀረበም:: የማሻሻያ እርምጃዎች አለመኖር የተከሰቱ ብልሹ

አሰራሮች እንደገና ለተቋሙ ስጋት የመሆናቸውን አጋጣሚ ስለሚያሰፋ እንደ ትልቅ ክፍተት ሊወሰድ ይችላል፡፡

- በዘርፉ ተቋማት ከፍተኛ መጠን ያለው ያልተወራረደ ሂሳብ መኖሩ የፋይናንስ መመሪያ ጥሰትን እንዲሁም የቁጥጥር ሥርዓት መላላትን አመላካች ሊሆን ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው፡፡

## 4.11. የተቋማት የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና

በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የአስተዳደር ዘርፍ ስር በሚገኙ ተቋማት ከፍተኛ የሙስና ስጋት (ተጋላጭነት) እንዳላቸው የተገለጹ አሰራሮችና ሂደቶች (processes) እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡-

- ነዳጅና ተሽከርካሪ አጠቃቀም እና የተሽከርካሪ ጥገና (የፌደራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን)
- የተሽከርካሪ ስምሪት (<u>መገለጫ</u>፡-የመንግሥትን ተሽከርካሪ ለግል ጥቅም ማዋል) (አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ፣ የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት)
- የኢንቨስትመንት ማበረታቻ አሰጣጥ (ኢንቨስትመንት ኮሚሽን)
- የኢንቨስትመንት ፈቃድና ምዝገባ (ኢንቨስትመንት ኮሚሽን)
- ለኢንቨስተሮች ድጋፍና ክትትል አሰጣጥ (ኢንቨስትመንት ኮሚሽን)
- የስደተኞች ምግብ እደላ (የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት)
- የስደተኛ ምዝገባ (የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት)
- ፈቃድ አሰጣጥ (<u>መገለጫ</u>፡- የቴክኒክ ብቃት ለሌላቸው ፈቃድ መስጠት) (የኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ባለስልጣን)

# ክፍል አምስት፡- ምክረ-ሀሳቦች

በዚህ ውስን ዳሰሳና ትንተና ጥልቅ ምክረ-ሃሳብ ማቅረብ ቢያስቸግርም የሚከተሉትን ጥቅል የመፍትሄ ሃሳቦች ለማቅረብ ተሞክሯል፡-

- በዘርፉ ተቋማት ውስጥ በተደጋጋሚ የዋጋ ማስተካከያ የተደረገባቸውና ተጨማሪ የስራ ውል የተሰጠባቸው በርካታ ፕሮጀክቶች መኖራቸው በጥናቱ ለማየት ተችላል፡፡ እነኚህ ፕሮጀክቶች ግዙፍ የሆነ በጀት የሚያንቀሳቅሱ ከመሆናቸው አንፃር የፕሮጀክት አስተዳደር አቅምን በማሳደግ የግንባታ ሂደት ለሙስና እና ብልሹ አሠራር እንዳይጋለጥ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡

- የፕሮጀክቶች በውሉ መሰረት በጊዜያቸው አለመጠናቀቅ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ እንዲሁም የህዝብን ሃብት ለብክነት የሚዳርግ በመሆኑ በፕሮጀክት ውል፣ ሂደትና ርክክብ ላይ ጥብቅ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፣

- በዘርፉ ተቋማት እጅግ ከፍተኛ መጠን ያለው ያልተወራረደ፣ ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳብ መኖሩን ጥናቱ አረጋግጧል። በዚህ ረገድ የተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት የሒሳብ አያያዝ እና ምዝገባን ወቅታዊና ትክክለኛ በሆነ መንገድ በማደራጀት የፋይናንስ ሂደትና ቁጥጥርን ውጤታማነት ለማጠናከር ካለው ፋይዳ አንፃር ተቋማቱ በቀጣይ አትኩረው ሊሰሩበት ይገባል።

- የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽንን እንደገና ለማቋቋም ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋሞቻቸው የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎችን በባለቤትነት የሚያስተባብሩ የሥራ ክፍሎች ሆነው እንደሚደራጁ ይገልፃል። ይህን ተልዕኮ በብቃት እንዲወጡ የሥነምግባር ክፍሎችን በተገቢው በጀትና የሰው ኃይል የተሟላ ማድረግ፣ ከሌሎች የሥራ ክፍሎች ጋር ያላቸውን ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር እንዲሁም የስራ ክንውናቸውን በበላይ ሃላፊዎች ማስገምገም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

- ግልፅ የበጀት ሂደትና አጠቃቀም መረጃ የመንግስት ገንዘብ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንደሚውል በህብረተሰቡ ዘንድ እምነት እንዲኖር ከማስቻሉ አንፃር፣ ተቋማቱ ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ የሚደረግበትን አሰራር ሊተገብሩ ይገባል። በተጨማሪም የኦዲት ሪፖርቶችን፣ ፀድቀው የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን እና መሰል ጉዳዮችን ለማህበረሰቡና ባለድርሻ አካላት በተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮች ተደራሽ በማድረግ የዘርፉ ተቋማት ግልፅነትና ተጠያቂነትን ማስፈን ይጠበቅባቸዋል።

- የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP) ስርአት ሃብትን በቁጠባ ለመጠቀምና የግዢ ሥርዓቱን በእቅድ ከመምራት አንፃር ያለውን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተቋማት የማዘመኑን ስራ በማጠናቀቅ ቀድሞ ከነበሩበት የማንዋል ሥራ ወደ ዲጂታል ሲስተም በፍጥነት እንዲዛወሩ ግፊት ያስፈልጋል።

- የሙስና ስጋትና የደንበኞች እርካታ ጥናቶች ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጡ የሚችሉ አሰራሮችን በመለየት ቅድመ-መከላከል ስትራተጂዎችን ለመቅረፅ እንዲሁም ተጠያቂነትን ለማስፈን ካላቸው ፋይዳ አንፃር ተቋማቱ በቀጣይ በመደበኛነት እና ወቅቱን በጠበቀ መልኩ እነዚህን ጥናቶች ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

- በዘርፉ ስር ባሉ ተቋማት ያለዕቅድ ግዢዎች፣ የቀጥታ ግዢዎችና ለአንድ አቅራቢ በተደጋጋሚ የሚሰጡ ግዢዎች እንደተስተዋሉ ማረጋገጥ ተችሏል። እነኚህ ግዢዎች እንዲካሄዱ የሚያስገድድ ህጋዊ መሰረት ሊኖር ቢሆንም የሙስና ስጋት ስለሆኑ ግዢዎቹ ለምን በግልፅ ጨረታ እንዳልተከናወኑ፣ ሳይታቀዱ እንደተገዙና ለምን ከአንድ አቅራቢ

በተደጋጋሚ እንደተገዙ አሳማኝ ምክንያቶች ሊቀመጥላቸው ይገባል፣ ዝርዝር ምክንያቶቹም ተደራሽ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

- የትምህርትና የስራ ልምድ የማጣራት ስራ በማከናወን ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ያለበቂ ዕውቀትና ችሎታ ተቋማቸውን በሚጎዳ ሁኔታ ተቀጥረው ከሚያገለግሉ ሰራተኞች የዘርፉን ተቋማት ማጥራት የግድ ይላል፡፡
- የዘርፉ ተቋማት አመራርና ሰራተኞች የታማኝነት፣ የተጠያቂነት፣ የፍትሃዊነት እና የመተማመን ጠንካራ የሞራል እሴቶችን እንዲያዳብሩ ባለመ መልኩ የሥነምግባር ስልጠናዎችን በመደበኛነት መስጠት ይጠብቅባቸዋል፡፡
- ተቋማት ውሎች ከመፈረማቸው በፊት በህግ ክፍል አስተያየት የሚሰጥበትን (የሚገመገምበትን) አሰራር ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የዘርፉ ተቋማት የተሽከርካሪዎች የጥገና አገልግሎት እና የነዳጅ አጠቃቀም አሰራር ላይ ተገቢውን የክትትልና ቁጥጥር ስርአት መዘርጋት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የኢንቨስትመንት ኮሚሽን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ አሰጣጥ፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድና ምዝገባ እንዲሁም ለኢንቨስተሮች ድጋፍና ክትትል አሰጣጥ ላይ ለሙስና ስጋት የሆኑ ክፍተቶችን በጥናት በመለየት የማሻሻያ እርምጃዎችን ሊወስድ ይገባል፡፡

## የማጣቀሻ ጽሑፎች


1. Chêne M. (2014). The Impact of Corruption on Growth and Inequality. https://www.transparency.org
2. CKB Kasser-Tee. (2020). Understanding, Preventing and Fighting Administrative Corruption in the Business Registration Regime in Ghana. Business Law Review, 41(4):134 – 138.
3. Clausen, Kraay and Nyiri. (2010). Corruption and Confidence in Public Institutions: Evidence from a Global Survey. Police Research Working Paper 5157. The World Bank.
4. David W. Simon, Sherbir Panag, Panag & Babu. (2017). Anti-Bribery Compliance Meets Permits, Approvals and Licences in India. IBA Anti-Corruption Committee Publication.
5. Esposito P. (2010). State Capture, Governance, Accountability in Companies and Local Public Administrations. Rirea, Milano: State Capture to Society Capture.
6. Folsom BW. (2003). The Myth of the Robber Barons: A New Look at the Rise of Big Business in America. Herndon, VA: Young America's Foundation.
7. International Monetary Fund and World Bank. (2012). "Revisiting the Debt Sustainability Framework for Low-Income Countries." Washington, DC.
8. Kaufmann, Montoriol-Garriga, & Recanatini. (2008). How Does Bribery Affect Public Service Delivery? Micro-Evidence from Service Users and Public Officials in Peru.
9. Klāvs Sedlenieks. (2003). Corruption in the Process of Issuing Building Permits, the Soros Foundation, Latvia.
10. Knies, E., Jacobsen, C., & Tummers, L. (2016). Leadership and organizational performance. In State of the art and research agenda: Routledge companion to leadership (pp. 404-418). Routledge.
11. OECD. (2017). Preventing Policy Capture: Integrity in Public Decision Making. OECD Public Governance Reviews.
12. OECD. (2017). Preventing Policy Capture: Integrity in Public Decision Making, OECD Publishing, Paris.
13. Shah A. (2007). Responsibility for Performance and the Fight Against Corruption. Washington, DC: The Work Bank.
14. Transparency International. (2010). Corruption in logging licenses & concessions, TI Working Paper # 03/2010.
15. Transparency International. (2013). Global Corruption Barometer. https://www.transparency.org/gcb2013

16. UN Development Programme – Oslo Governance Centre. (2004). The Impact of Corruption on the Human Rights Based Approach to Development.
17. World Bank. (2012). Fighting Corruption in Public Services: Chronicling Georgia's Reforms.
18. Zain, Sabri. (2020). Corrupting trade: An overview of corruption issues in illicit wildlife trade. TNRC Introductory Overview.